ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ
Wisdom at the source of the Blue Nile

# ናይል
# THE NILE



ኢ.-ሜይል፡- bduinfo63@gmail.com or gracetsegi@gmail.com ድረ-ገጽ፡- http://www.bdu.edu.et የፌስቡክ ገጽ፡- www.facebook.com/bduethiopia

ናይል 4ኛ ዓመት፣ ቁጥር 1፣ የካቲት 2008

## የመመመ ቡድኖች በራዕይ ጥበብ 2017

በባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)

## “ነፃ አውጪው” ማን ነው? ቅኝ ገዢ፣ ነፃ አውጪ መሆን ይቻለዋልን?

ከባለፈው ወር እትም የቀጠለ
ጀማል ሙሀመድ (ዶ/ር)

## A Closer Look at Distance Education at BDU

Yenus Nurie

## Save the Oxen for Your Survival

Chalachew Tarekegne

## ግፊት ሲገፋ

ሂሩት አድማሱ






BDU celebrates the 120th commemoration of Adwa victory





ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከንግዱ ማኅበረሰብ ጋር ውይይት ሲያካሂድ





BDU’s female vice president appointment

እውነትን መፈለግና ለሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!

ናይል
THE NILE

# Bahir Dar University

## Motto of Bahir Dar University

“Wisdom at the Source of the Blue Nile”

“ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ”

## Vision

The vision of Bahir Dar University is to become one of the ten premier research universities in Africa by 2025.

## Mission

The mission of Bahir Dar University is to contribute substantially to the nation and beyond through high quality education, research and community services.

### Core Values

- Quality
- Discourse
- Innovation
- Integrity
- Democratic culture
- Social responsibility


## ናይል ጋዜጣ

በኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት
የውስጥ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ክፍል
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

**የአማካሪ ቦርድ አባላት**

ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ
ዶ/ር ጌታቸው ፍስሃ
አቶ እምቢያለ በየነ
አቶ አማረ ካሳው
አቶ በላይነህ ወርቁ
ዶ/ር አልማዝ ጊዜው
አቶ ፈታሒ በቃሉ
ወ/ሮ መድኃኒት በላቸው
አቶ ቴዎድሮስ ካሳዬ

**ዋና አዘጋጅ፡-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ም/ዋና አዘጋጆች**
ሂሩት አድማሱ

**አርታኢዎች**
አብነት ሰለሞን
የኑስ ኑሬ

**ግራፊክስና ሌይአውት፡-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ዘጋቢዎች፡-**
የማነ ገብሩ
ታድዬ አስማረ
አምሳሉ ጥላሁን
ትዕግስት ዳዊት
ሙሉጎጃም አንዷለም

**አምደኞች፡-**
ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
ወንያ ዛን(ዶ/ር)
ሂሩት አድማሱ
የኑስ ኑሬ
ቻላቸው ታረቀኝ
ቤተልሄም ሃይለማርያም

**ፎቶ አንሺዎች፡-**
ታምራት አታላይ
ሙሉጌታ ዘለቀ

**የኮምፒውተር ጽሁፍ፡-**
ታሪክ ታደሰ
የሻለም መንግስቴ
ፋንታነሽ ላቀው

**ትራንስፖርት፡-**
ማናለ ኃይሌ

**መልእክተኞች፡-**
ንብረት ታፈረ
አለምነሽ ሙሉ


ስልክ፡- +251 583206088
+251 583207023

## ርዕሰ-አንቀጽ

# የታሪክ አደራችንን በፅናት በመወጣት ሀላፊነታችንን እንወጣ!!!

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በያዝነው ወር 120ኛውን የአድዋ የነጻነት ድል የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብና ጥሪ የተደረገላቸው አረበኞች በተገኙበት በድምቀት አክብሯል። በበአሉ ላይ የአሁኑ ትውልድ ከአባቶቹ የተቀበለውን አደራ በፅናት መወጣት እንዳለበትና የበለጠ ታሪክ እንዲሰራ አደራ እንዲቀበል ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነው። ለሀገራዊ የልማትና እድገት ግስጋሴ መሰረት የሆነው የአድዋ ድል በዓል የኢትዮጵያ ሕዝቦች ቃል ኪዳናቸውን የሚያድሱበት፣ የሕዳሴ ጉዞአቸውን አፈፃፀም የቃኙበትና ለተሻለ አፈፃፀምና የጋራ ተጠቃሚነት ቁርጠኝነታቸውን የሚያረጋግጡበት መሆን አለበት። የሁሉም የሀገሪቱ ዜጐች የነቃ ተሳትፎ አስፈላጊ መሆኑ በበዓሉ ላይ አድንኦት ተሰጥቶታል።

አባቶቻችን ክንዳቸውን አበርትተውና በዓላማ ፀንተው ሀገራችንን ከቅኝ ግዛት ነጻ አድርገዋል። ብሔራዊ ማንነታቸውንና ክብራቸውን በተጋድሎአቸው ጠብቀው በማቆየት ሀገራቸውን የጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ተምሳሌት አድርገዋል። ከሀገራቸው ሉዓላዊነት፣ ከነፃነታቸውና ከማንነታቸው በላይ አንዳችም ነገር የማያስቀድሙት የሀገራችን ሕዝቦች ባላቸው የረጅም ዘመን የነፃነትና የተጋድሎ ታሪክ ዓለምን አስደምመዋል። በአድዋና በሌሎች ጦርነቶች ላይ በወራሪዎችና ፋሺሽቶች ላይ የተጐናፀፏቸው ድሎች የጥቁር ህዝቦች የነፃነት ተምሳሌቶች ሆነው የዘመናትን ድንበር ዘልቀዋል። በነፃነት ወዳድነታቸውና የአንድነት ፅናታቸው ለዚህ አኩሪ ገድል የበቁት ኢትዮጵያዊያን መቼም ቢሆን በሀገራቸው ሉዓላዊነት ላይ የተደራደሩበት አጋጣሚ ተፈጥሮ አያውቅም።

የአሁኑ ትውልድም የአባቶቹን የጋራ ጠላትን በጋራ የመመከት እና አሳፍሮ የመመለስ አኩሪ ባህል በማስቀጠል የእድገት እንቅፋት የሆነውን ርሀብና ድርቅ ለማስወገድ በጋራ መነሳት ይኖርበታል። በአባቶቻችን የፀናው የትግል አቋም ለጋራ እድገታችንና ዘላቂ ተጠቃሚነታችንን በአንድነትና በቁርጠኝነት መስራት ይጠበቅብናል። ሁሉም በተሰማራበት መስክ ውጤታማ በመሆን የሚጠበቅበትን ሀላፊነት መወጣት ይኖርበታል። ትውልዱ በተለይ የተማረው ክፍል ትኩረቱን ወደ ልማትና እድገት በመቀየር የሀገሪቱን የድህነትና የርሀብ ታሪክ በመቀየር የሚጫወትው ሚና ከፍተኛ መሆን አለበት።

በርካታ ምሁራንን ያፈራውና እያፈራ ያለው ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲም ታሪካዊ ሁነቶችንና ክንውኖችን በትክክለኛ መረጃ ላይ በመመርኮዝ ዝክረ በአሉን በማክበር የአሁኑ ትውልድ የሚጠበቅበትን አደራ በማሳወቅ ሀላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል። በዘርፉ የተሰማሩ ምሁራን በምርምር የተደገፈ እውቀቶችን በመተንተን፣ ትርጉም በመስጠትና እውነታውን በመለየት ለማህበረሰቡ ትክክለኛ መረጃዎችን ማድረስ ይጠበቅባቸዋል። ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ሀገራዊው የለውጥ ሽግግር ሂደት እውቀትን ማዕከል አድርጐ እንዲከናወንና ፍፃሜው የተሳካ እንዲሆን ያልተገደበ ተሳትፎአቸው ወሳኝነት አለው። የዩኒቨርሲቲያችን ማህበረሰብም ይህንን ሀላፊነት በመወጣት የሚጠበቅበትን ለማበርከት ዝግጁ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ እናረጋግጣለን።

To follow the
latest news about BDU, check out
our
website:-
**http://www.bdu.edu.et**
facebook page:-
**www.facebook.com/bduethiopia**

## ቁልፍ መልዕክት

# የመመመ ቡድኖች በራዕይ ጥበብ 2017

ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት

ዩኒቨርሲቲያችን የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለመሆን የራዕይ ጥበብ 2017ን መስመር እየተከተለ መሆኑ ይታወቃል። ይህ መስመር ግልጽ መዳረሻ ግብ ያለውና ከግቡ ለመድረስም ግልጽ ስትራቴጂካዊ ስልቶች ተለይተው በመተግበር ላይ ናቸው። ከእነዚህ ስትራቴጂካዊ ስልቶች አንዱ ሁሉንም ተግባሮች በተደራጀ የመመመ (የመማር የመመራመርና የመተግበር) ቡድኖች መፈፀም የሚለው ነው። የመመመ ቡድኖች አመሠራረትና አሠራር ዩኒቨርሲቲው ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ባሰራጨውና በሚተገብረው የለውጥ ፕሮግራም ሰነድ ላይ ቀርቧል። የዚህ አጭር ጽሑፍ አላማ የአመራሩ፣ የመምህራን፣ የአስተዳደር ሠራተኞችና የተማሪዎች የመመመ ቡድኖችን የተግባር አፈፃፀሞች የምንመዝንባቸውን ሶስት መሠረታዊ መለኪያዎችን በመግለጽ የሚመለከታቸው አካላት በነዚህ መመዘኛዎች ራሳቸውን እንዲመዝኑና ሌሎች አካላትም እንዲመዝኗቸው በግልጽ እንዲታወቅ ለማድረግና መመዘኛ ነጥቦች ላይም ውይይቶች እንዲነሡና በሂደት የሚዳብሩበትን መንገድ ለማመቻቸት ነው።

የመመመ ቡድኖች የተግባር አፈፃፀም የሚመዘነው፡-

I. በዕቅድ ከመገናኘት፣
II. የተሰጠን ኃላፊነትንና ተግባርን መሠረት አድርጐ ከመወያየትና መፍትሄ አቅጣጫ ከማስቀመጥ፣
III. በተቀመጠው የመፍትሄ አቅጣጫና የተግባር ስምሪት አንፃር ከመተግበር /ውጤት ማምጣት/ አኳያ ነው። በተራ ቁጥር I እና II የተቀመጡት መመዘኛዎች ከመማርና ከመመራመር አንፃር የሚታዩ ናቸው።

አመራሮች ሲገናኙ የሚወያዩትና የመፍትሄ አቅጣጫ የሚፈልጉት ከሚመሩት ዘርፍ አንፃር ያሉ ተጨባጭ ችግሮችን ለመፍታት ነው። በግዥ መጓተት የተፈጠረ ተጨባጭ የቤተ-ሙከራ ወይም የቢሮ ችግሮች ካለ ግዥውን በምን መንገድ በማሳካት ችግሮች ሊፈቱ ይችላሉ? ብሎ መፍትሄ ማስቀመጥ ለአመራሩ ምርምር እንደማድረግ ሊታይ ይችላል። መምህራን ተማሪዎቻቸው በስርዓተ ትምህርቱ የተቀመጠውን ዕውቀትና ክህሎት እንዲጨብጡ በምን ዘዴ ላስተምራቸው? ምን አይነት የተግባር ትምህርት እንዲሠሩ ላድርግ? የሚፈለገውን ዕውቀትና ክህሎት መያዛቸውን በምን የፈተና ዘዴ ላረጋግጥ? ብለው ሲወያዩ እነዚህ መምህራን በመመመ ቡድኖቻቸው የመማርና የመመራመር ስራ እየሠሩ ነው ማለት ይቻላል። ተማሪዎችም በመመመ ቡድኖቻቸው ሲገናኙ የተማሯቸውን ጭብጦች በማንሳት በንድፈ ሀሳብ ምን እንደተማሩ፣ ንድፈ ሀሳቡ ያለውን አንድምታና በተለይ በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ሊኖር የሚችለው ጠቀሜታ ላይ ሲወያዩ እየተማሩና እየተመራመሩ ነው ማለት ነው። በዚህ አግባብ ለሁሉም ዘርፎች ከተሰጣቸው ተልዕኮ አንፃር በማያያዝ ከመማርና መመራመር አንፃር የሚጠበቅባቸውን ስራዎች ማስቀመጥ ይቻላል።

በሳይንስ አንድን የቆመ ህንፃ ወይም ሀውልት ሲገፉ ቢውሉ ህንፃው ወይም ሀውልቱ በተወሰነ ርቀት ቦታ ካልቀየረ ምንም ስራ እንዳልተሠራ ይቆጠራል። በተመሳሳይ መልኩ የመመመ ቡድኖች በዕቅዳቸው ተገናኝተውና ከላይ በጠቀስነው መሠረትም ከተልዕኳቸው አንፃር ተወያይተው ውጤት ካላመጡ ከንቱ ልፋትና ቡድኖቹም እንደሌሉ ይቆጠራል። የመመመ ቡድኖች የተደራጁትና በዕቅድ እየተገናኙ እንዲወያዩ የተፈለገው ለብቻ በመስራት ማምጣት የማይችሉትን ውጤት በጋራ እንዲያመጡት ነው። በመሆኑም የተቋቋሙበት ዋነኛ ግብ ተልዕኳቸውን ለማሳካት ነው። የአመራሩ የመመመ ቡድኖች (የም/ፕሬዚዳንቶች ፎረም፣ የዲኖች ፎረም፣ የዳይሬክተሮች ፎረም፣ የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች ፎረም) ችግሮችን የማይፈቱና የሚጠበቅባቸውን ውጤቶች የማያስመዘግቡ ከሆነ ትርጉም የለሽ የሰዎች ስብስብ ይሆናሉ። በዚህም በተደራጀ የመመመ ቡድኖች ተግባሮችን እያስፈፀሙ የራዕይ ጥበብ 2017ን ግብ ሊያሳኩ አይችሉም።
በተመሳሳይ ሁኔታ የመምህራን የመመመ ቡድኖች ለተማሪዎች የሚጠበቀውን ዕውቀትና ክህሎት ለማስጨበጥ የሚያስችሉ አደረጃጀቶች ካልሆኑ ትርጉም የለሽ የመምህራን ስብስቦች ይሆናሉ ማለት ነው። ተማሪዎችም በራሳቸው የመመመ ቡድኖች እርስ በርሳቸው ዕውቀትና ክህሎት ለመገንባት የማይጠቀሙባቸው ሊሆኑ አይገባም።

የሁሉም የመመመ ቡድኖች ትኩረት ከተሰጣቸው ተልዕኮ አኳያ አመርቂ ውጤት ማስመዝገብ ነው። በመሆኑም ሲወያዩ ግልጽ የተግባር ስምሪት ይዞና አስይዞ ተግባራዊ በማድረግ የሚጠበቀውን ውጤት ማስመዝገብ ላይ ልዩ ትኩረት ማድረግ ወሳኝ ነው።

የዩኒቨርሲቲያችን ማህበረሰብና ሌሎች አካላት የዩኒቨርሲቲያችንን የመመመ ቡድኖች ከላይ በአጭሩ በገለጽናቸው እሳቤዎች መሠረት እንዲገመግሟቸውና ለቀጣይ መሻሻል ግብዓት እንዲሠጡን በአክብሮት እንጋብዛለን። ሁሉም የመመመ ቡድኖች በዚህ አጭር ጽሑፍ የውጤት እይታዎች ላይ የራሳቸውን አስተያየት በመስጠትና በመወያየት እንዲያዳብሩት እንጋብዛለን።

ራዕይ ጥበብ 2017ን እናሳካለን!

### ውድ የናይል ጋዜጣ አንባቢያን

በናይል ጋዜጣ ለቀጣዩ ወር ዕትም ጽሁፍ ማበርከት የምትፈልጉ ሁሉ አዲሱ ጥበብ ህንጻ 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 512 በሚገኘው ቢሯችን ድረስ በመምጣት ወይም በኢሜል gracetsegi@gmail.com በኢሜል አድራሻችን በመላክ ወይም በአካል በመምጣት መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን።
ዝግጅት ክፍሉ

# አበይት ዜናዎች...

## 120ኛው የዓድዋ የድል በዓል በዩኒቨርሲቲው ተከበረ

በሙሉጎጃም አንዱዓለም

120ኛው የዓድዋ የድል በዓል "ዓድዋና ኢትዮጵያዊነት" በሚል መሪ ቃል በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፔዳ ግቢ የዩኒቨርሲቲው መምህራን፣ አስተዳደር ሰራተኞች፣ ተማሪዎችና እንዲሁም አርበኞችና ሌሎች ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት በደማቅ ስነስርዓት ተከበረ፡፡

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ የመክፈቻ ንግግር ባደረጉበት ወቅት መርኃ ግብሩን ላዘጋጁት አካላት ምስጋና ካቀረቡ በኋላ የዓድዋ የድል በዓል ከ120 አመት በፊት ለነፃነታችን ዉድ ህይወታቸውን የከፈሉና ያለፉ ትውልዶችን በመዘከር ቀደምት ኢትዮጵያዊያን የገጠማቸውን ችግር ለመፍታት ያደረጉት ታላቅ ተጋድሎ፣ ዉጊያውና ድል የማድረጋቸው ምስጢር ምንነት የምንማርበት ብሎም ለዛሬውና ለቀጣዩ ህይወታችን ቁምነገር የምንይዝበት ነው ብለዋል፡፡

ዶ/ር ባይሌ በንግግራቸው እንዳሉት ዛሬ የዓድዋን በዓል የሚያከብር ትውልድ ድህነትን በማሸነፍ፣ ግዙፍ የቴክኖሎጂ አቅም በመፍጠር ለሀገሩ እድገት ትልቅ አስተዋፅኦ በማድረግ ለታሪክ ተረካቢው መጭ ትውልድ አርአያ ሆኖ ማለፍ እንዳለበት አሳስበዋል፡፡

የዓድዋ ድልን በተመለከተ ገለፃ ያደረጉት የቀድሞ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፍልስፍና መምህርና ተመራማሪ ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ ዩኒቨርሲቲዎች ታሪክን ለማቆየት ያላቸው ሚና እጅግ ከፍተኛ መሆኑን አውስተዋል፡፡ ዶ/ር ዳኛቸው አክለውም ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በተለይ በባህል፣ በቅርስና በታሪክ እንክብካቤ፣ ጥበቃና ጥናት ዙሪያ የሚሰራውን ስራ አድንቀዋል፡፡

በታሪክ ምሁራኑ በዶ/ር ሳምሶን ጫኔ እና በአቶ ዳንኤል መሰረት 'The legacy of the victory of Adwa' እና 'Discourses on the Battle of Adwa the images of Ethiopia thereof' በሚሉ ርዕሶች ጥናታዊ ጽሁፎች እንዲሁም 'ዓድዋ እንደገና' በሚል ርዕስ የስነ ጽሁፍ መምህርት በሆኑት በወ/ሮ ሂሩት አድማሱ ለታዳሚዎች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡

የመርኃ ግብሩ ታዳሚዎች ስለ በዓሉ አከባበር እና ስለ ጀግኖች አርበኞች ያላቸውን ሀሳብና ጥያቄዎችን አቅርበው ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ በስነ ስርዓቱ ላይ ድሉን የሚያስታዉስና ስሜት ቀስቃሽ ሽለላና ፉከራ በዩኒቨርሲው ባልደረባ አቶ መኳንንት ከተማ ቀርቧል፡፡ የአማራ ክልል ፖሊስ ማርሽ ቡድን በባሕር ዳር ከተማ ዋና ዋና መንገዶች ጀምሮ እስከ ዩኒቨርሲቲው ግቢ ድረስ የድል ጣዕመ ዜማዎችን ማራኪ በሆነ መልኩ በማቅረብ ለበዓሉ ድምቀት ሰጥቶታል፡፡

## ዩኒቨርሲቲው ከንግዱ ማኅበረሰብ ጋር ውይይት አካሄደ

በሙሉጎጃም አንዱዓለም

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በባሕር ዳር ከተማ ውስጥ ከሚገኙና ለዩኒቨርሲቲው አገልግሎት ከሚሰጡና የተለያዩ ሸቀጣ ሸቀጥ ከሚያቀርቡ የንግድ ማኅበረሰብ አካላት ጋር ውይይት አደረገ፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ መድረኩን ያዘጋጁትን አካላት ካመሰገኑ በኋላ የውይይቱን ወቅታዊነት፣ አስፈላጊነቱንና ለጋራ ለውጥ አብሮ ለመስራት መግባባት የሚደረስበት እንደሚሆን ምኞታቸውን በመግለፅ ውይይቱን በይፋ ከፍተዋል፡፡

ዶ/ር ባይሌ ዩኒቨርሲቲው ግልፅ አሰራርና ከሙስና የፀዳ የግዥ ስርዓት ለማስፈን እየሰራ መሆኑን ገልፀው ዩኒቨርሲቲው በሚያካሂዳቸው ግዢዎች ላይ ስላሉ ጠንካራ ጎኖችና መስተካከል ስለሚኖረባቸው ጉዳዮች ከንግዱ ማኅበረሰብ ጋር ለመወያየት እንዳስፈለገ ተናግረዋል፡፡

ለውይይት መድረኩ መነሻ የሚሆን ጽሁፍ ያቀረቡት የውጭ ግንኙነትና ፓርትነርሽፕ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ሞገስ አብርሃ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከተለያዩ ተቋማት፣ ድርጅቶችና የማኅበረሰብ አካላት ጋር ስለመሰረታቸው ግንኙነትና ስለሚሰራቸው የትብብር ሥራዎች ተንትነዋል፡፡

የውይይቱ ተሳታፊዎች ከዩኒቨርሲቲው ጋር ስለነበራቸው የግብይት አካሄዶች አስተያየት የሰጡ ሲሆን ለወደፊት ተጠናክረው መቀጠል ስላለባቸው ጉዳዮች እንዲሁም መሻሻል ስለሚኖርባቸው አንዳንድ ጉዳዮች ላይ ሀሳብ ሰንዝረዋል፡፡ ተሳታፊዎች ለወደፊት ከዩኒቨርሲቲው ጋር በጋራ በማቀድና በጋራ በመፈፀም ግልፅና ከአድሎአዊ አሰራር የነፃ የግብይት ስርዓት ለመዘርጋት መግባባት ላይ እንዲደረስ ከፍተኛ ፍላጎት አሳይተዋል፤ ድጋፍ እንደሚያደርጉም አረጋግጠዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ አመራሮች በዩኒቨርሲቲው አሰራርና ከንግዱ ማሕበረሰብ ጋር ስላለው ግንኙነት በተመለከተ በተሳታፊዎች ለተነሱት ጥያቄዎች ላይ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

በውይይቱ ላይ የንግዱ ማኅበረሰብ፣ ከዩኒቨርሲቲው ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የመጡ የግዥ ባለሙያዎች፣ ከክልሉ የአሰሪዎች ፌዴሬሽን እንዲሁም ከባሕር ዳር ከተማ ንግድ ምክር ቤት የመጡ ተጋባዥ እንግዶች ተሳትፈዋል፡፡

## ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሴት ምክትል ፕሬዝዳንት ሾመ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ቦርድ የካቲት 19/2008 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ዶ/ር ሙሉነሽ አበበን የዩኒቨርሲቲው የምርምርና ማኅበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዝዳንት ሆነው እንዲያገለግሉ ሾሟል፡፡ በዩኒቨርሲቲው ዋና ግቢ በተካሄደ ስነ ስርዓት ላይ ዶ/ር ሙሉነሽ ከተሰናባቹ ምክትል ፕሬዝዳንት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራው ስራቸውን በይፋ ተረክበዋል፡፡

ዶ/ር ተስፋዬ በስነ ስርዓቱ ላይ ንግግር ባደረጉበት ወቅት በኃላፊነት በነበሩበት ጊዜ በሙሉ ከዩኒቨርሲቲው አመራርና ማኅበረሰቡ ጋር የነበራቸው ቀና ግንኙነት ለስራቸው መልካም አጋጣሚ እንደፈጠረላቸው በመግለፅ ምስጋናቸውን አቅረበዋል፡፡ በመቀጠልም ለዶ/ር ሙሉነሽ የእንኳን ደህና መጣሽ የመልካም ምኞት መልዕክታቸውን ካስተላለፉ በኋላ ለወደፊትም ቢሆን ዩኒቨርሲቲውን ባላቸው ሙያ ለማገልገል ዝግጁ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

ዶ/ር ሙሉነሽ በበኩላቸው ሹመቱ ከፍተኛ ስራ መስራት የሚጠብቅና የህዝብ አደራቸውን የሚወጡበት እድልና አደራም ጭምር በመሆኑ የሚጠበቅባቸውን ሁሉ እንደሚያደርጉና ዩኒቨርሲቲው የጀመረውን የለውጥ ጉዞ በማስቀጠል ሀገርን የሚጠቅም ስራ እንደሚሰሩ ቃል ገብተዋል፡፡

በስነ ስርዓቱ ላይ ዩኒቨርሲቲውን በተለያየ ጊዜ በምክትል ፕሬዝዳንትነት ያገለገሉ ምሁራን በአመራርነት ዘመናቸው ስለነበራቸው ተሞክሮ ለታዳሚዎች ገለፃ አድርገዋል፡፡ የዩኒቨርሲቲዉ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ እንዲሁም አሁን በምክትል ፕሬዝዳንትነት በስራ ላይ ያሉ አመራሮች ለተሰናባቹ ለዶ/ር ተስፋዬ ምስጋናቸውን እንዲሁም ለተሿሚዋ ዶ/ር ሙሉነሽ የመልካም ምኞት መግለጫ አስተላልፈዋል፡፡

ዶ/ር ሙሉነሽ ከማስተማርና ከመመራመር በተጨማሪ በተለያዩ ኃላፊነቶች ዩኒቨርሲቲውን ሲያገለግሉ የቆዩ ምሁር መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ሹመቱ ዶ/ር ሙሉነሽን በዩኒቨርሲቲው ታሪክ ሁለተኛዋ የሴት ምክትል ፕሬዝዳንት ያደርጋታል፡፡ ዩኒቨርሲቲው ከዚህ ቀደም በዶ/ር የሺመብራት መርሻ ምክትል ፕሬዝዳንትነት በኋላም በፕሬዝዳንትነት ሲተዳደር እንደነበረም ይታወሳል፡፡

## መማር ማስተማሩን በምርምር በመደገፍ የትምህርት ጥራቱን ማስጠበቅ እንደሚቻል ተገለፀ

በታድዬ አስማረ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ በቋንቋ፣ ባህልና ሥነ-ተግባቦት የሚያካሂደውን አውደ ጥናት መማር ማስተማሩን በምርምር በመደገፍ የትምህርት ጥራትን ማስጠበቅ እና በዘርፉ የሚታዩ የማህበረሰቡ ችግሮች ለመፍታት ተደራሽ ማድረግ በሚል አላማ 3ኛውን ሀገር አቀፍ አውደ ጥናት አካሄደ፡፡

የዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ማተቤ ታፈረ አውደ ጥናቱን ሲከፍቱ እንደገለፁት በ2017 የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለመሆን የያዘውን ራዕይ ለማሳካት ምርምሮች እንዲሠሩ ከፍተኛ በጀት መድቦ እየተንቀሳቀሰ እንደሚገኝና የምርምር ማዕከላት በማቋቋም መምህራን በተመረጡ የምርምር አቅጣጫዎች በቡድን ተቀናጅተው ምርምር እንዲያካሄዱ እያደረገ ይገኛል፡፡ የተሰሩ ምርምሮች ለማህበረሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑ ሀገር አቀፍና አለም አቀፍ አውደ ጥናቶችን ከማዘጀት በተጨማሪ በህትመት እየታተሙ ማህበረሰቡ እንዲያውቃቸው እየተደረገ እንደሚገኝ ዶ/ር ማተቤ ተናግረዋል፡፡

የሂዩማኒቲ ፋኩልቲ ዲን ዶ/ር ስዩም ተሾመ በበኩላቸው የአውደ ጥናቱ መዘጋጀት መማር ማስተማሩን በምርምር

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

## መፅሐፍ ተመረቀ

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ ሳምንታዊ ሴሚናር ላይ በአቶ ቴዎድሮስ ተፈራ የተጻፈ The Anatomy of ATP and other Essays በሚል ርዕስ መጽሀፍ የፋኩልቲው መምህራን በተገኙበት ተመርቋል፡፡

የመጽሀፉ ጠቅላላ ይዘት በፋኩሊቲው መምህራን በዶ/ር ተስፋዬ ዳኜው፣ በዶ/ር አየነው ጓዴ እና በዶ/ር ጥላሁን በጅቷል አማካኝነት ዳሰሳ የተደረገ ሲሆን የመጽሃፉ ደራሲ አቶ ቴዎድሮስ መጽሃፉን ለማጻፍ መነሻ የሆናቸውን ምክንያት አቅርበዋል፡፡ መጽሃፉ ለመምህራንና ለተማሪዎች አጋዥ እንደሚሆን እና የጸሃፊው ተነሳሽነት የሚበረታታ መሆኑን በምርቃቱ ላይ የተገኙ ተሳታፊዎች ገልጸዋል፡፡

አቶ ቴዎድሮስ ይህ ሁለተኛ መጽሀፋቸው ሲሆን ከዚህ በፊት Journey of a passion የተሰኘ ልብወለድ መጽሀፍ አሳትመው ለአንባቢ አቅርበዋል፡፡

# ግፊት ሲገፋ

በሂሩት አድማሱ

የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነጽሁፍ ት/ክፍል - የስነጽሁፍ መምህርት

nanihira@gmail.com

መታሰቢያ የዓመታት ናፍቆቱ እውን ሊሆን ተቃርቧል። በዚህ ሰዓት ፍጹም ደስታ ሊሰማው ሲገባ በፍርሃት ተውጧል። ‹ምናለ እንደወትሮአችን ሳንለያይ ፍቅርን እያጣጣምን በኖርን። አልቻልንማ! ሰው አላስቀምጥ አለን። በተለይ የኔ እናት ትብሳለች። ሮሚን በወጣች በገባች ቁጥር ትጨቀጭቃት ነበር። በየሰርግ በየክርስትናው ባገኘቻት ቁጥር ትወተውታት ነበር።› እያለ ከራሱ ጋር ማውት ጀምሯል። ሮሚ ሰው ማስቀየም የማትወድ መከፋቷን ዋጥ አድርጋ የሚትኖር ፈገግታና ሳቅ ብቻ ምግቧ የሚመስሉ ወጣት ቀንበጥ ናት። ሮሚና ከመታሰቢያ ከተጋቡ አምስት ዓመት ቢሆናቸውም ልጅ አልነበራቸውም።

እንደተጋቡ ሰሞን ልጅ ያስፈልገናል ብለው ስላላመኑ ለተወሰኑ ወራት የወሊድ መቆጣጠሪያ ሮሚ እንድትጠቀም ተስማምተው በስምምነታቸው መሰረት ሮሚ ተጠቅማ ነበር። መንፈቅ እንዳለፋቸው ግን የመታሰቢያ እናትም ሆኑ የሷ ቤተሰቦች ሆድ ሆዷን እያዩ ‹‹ምነው ምንም የለም እንዴ? ብቻ መቆጣጠሪያ እየተጠቀምኩ ነው እንዳትይ!›› ብለው ሲያፋጥጧት እርግፍ አድርጋ ተወችው። ልክ እንደሌሎቹ ሁሉ እሷም ማርገዟን በጉጉት መጠባበቅ ጀመረች። አንድ ወር፤ ሁለት.. ሶስት እያለ አራት ዓመታት ነጎዱ።

‹‹እኔ አሁንስ መቲ መሮኛል። በተለይ የአንተ እናት እኔን ባዩ ቁጥር የሚናገሩኝ ነገር ያበሳጨኛል።››

‹‹ተያት እማዬን የምታውቂያት ናት። የልጅ ልጅ ያላየች ይመስል ባገኘችን ቁጥር መወትወት ትወዳለች። አዲስ ነገር ነው እንዴ ሮሚ?››

«የሚገርም ነው እኔ ጠፍጥፌ እሰራው ይመስል በእግዜር ስራ የሚኮንኑኝ ለምንድን ነው? ፈጣሪስ ለምን ዝም አለኝ?» እንባዋ ሁለት ጉንጮቿን አርሰው እየነጠሩ ጡቶቿ ላይ ያርፉ፣ ልብሷንም ያርሱ ጀመር።

«ኧረ ሮሚ በፈጠረሽ ምን ያስለቅስሻል። ይህ እኮ እግዚአብሔር ሲፈቅደው የሚሆን እንጂ እኛ ስለፈለግን የሚመጣ አይደለም። በቃ እኛ በማንሰራው ስራ ተጠያቂ አይደለንም። ይልቅ ቤታችን በዚህ የተነሳ አይቀዝቅዝ እንደቀድሞው በፍቅራችን ይሙቅ።» ለማረሳሳት መኮርኮር ጀመረ ሳቅና ጨዋታው ደራ። በቃ ሮሚ ሲበዛ የዋህ ስለሆነች ነገር አታከርም። ቶሎ ስሜቷ ይነካል በቶሎ ትግላለች። የመታሰቢያ ማግባቢያ፣ ቀልድና ልፊያ ሲጀምር ግን ወዲያ ትለወጣለች፣ እንደገና እየፈካች ውበቷ እየወጣ ይመጣል።

መታሰቢያ ይህን ሁሉ እያሰበ ሮሚ የተኛችበት ክፍል ከአሁን አሁን ተከፈተ እያለ ይጠባበቃል። ሆስፒታሉ የታወቁ የህክምና ዶክተሮች ያሉበት፣ በሰለጠኑ ባለሙያዎችና በተሟላ ቁስ የተደራጀ መሆኑን ሲያይ ልቡ ይረጋጋለታል። የሮሚ ድምጽ እየቀነሰ መምጣቱ እና ለወሬ ነገራ እንኳ ብቅ የሚል ሰው መጥፋቱን ሲያስተውል ጭንቀቱ ሊውጠው ይደርሳል። «ህይወት በምድር ላይ ብርቱ ሰልፍ ናት ያለው ማን ነበር?» ከዚህ ሁሉ ጭንቅ በቀረበን ኖሮ ሰላማዊ ህይወታችንን እየኖርን ብንቆይ ምን ነበረበት?»

እናቱ ታወሱት፤ ጎረቤቶቹ ውል አሉበት፤ ተናደደባቸው። በየእለቱ ከሮሚ ጋር በገባ በወጣ ቁጥር የሚያነሱት ጥያቄ የሚሰጡት አስተያየት ያበሸቀው ነበር። በየማሕበራዊ አጋጣሚው ሰው በተሰበሰበበት ሁሉ ጉዳዬ ብለው የሚነተርኩት ቀረብንህ ባዮች በተለይ ደግሞ የእናቱ ወቀሳ አዘል ንግግር ያናድደዋል።

የወንድሙ ሰርግ ዕለት መናፈሻ ውስጥ እያሉ መታሰቢያና ሮሚ ተነጥለው በሳቅና በጨዋታ ፈክተው ይዝናናሉ። የመታሰቢያ እናት የተለመደውን ንትርክ ጀመሩ።

«እኔ የምለው የእናንተ ሙሽርነት የሚያበቃው መቼ ነው። በየሰርጉ ሙሽራ እየሆናችሁ መታየት አይበቃችሁም። እስቲ ልብ ግዙ። ልጅ ውለዱና ከበድ ከበድብድ በሉ።»

«እማዬ ምን ነካሽ። የጆን ሰርግ እኮ ነው! ይህን ጉዳይ እዚህ ምን አመጣው?

«ናፍቄ ነዋ። ልጅ ወልደህ ማየት ፈለኳ፣ የልጄን ልጅ።»

«ሞልተውሻል የልጅ ልጆች እነሱ አይበቁሽም።»

«የእነሱ ሌላ የአንተ ሌላ።»

ሮሚ ከዚህ በላይ መስማት አልፈለገችም። ሰውን ሁሉ አቆራርጣ ብቻዋን እያለቀሰች መሮጥ ጀመረች

መታሰቢያም በእናቱ እያዘነ ሮሚን ተከተላት። ርቃ አልራቀችውም ነበርና ደረሰባት።

«ሮሚ እማዬ እኮ ልማድ አድርጋው ነው አትፍረጂባት።»

« ለራሴ ነው የማለቅሰው። ምናለ ካንተ እግዜር ልጅ ሰጥቶ እኔን ቢገላግለኝ ወይም ቢወስደኝ።»

«ሮሚ ምን እያልሽ ነው? ከልጅ አንቺ ትበልጪብኛለሽ እኮ! እንደዚህ አትበይ። ለሚናገሩት ነገር ስፍራ አትስጪ ነው የምልሽ። ቆይ አንድ ጥያቄ ልጠይቅሽ። ከእኔ የምትወልጂውም ልጅ ትወጃለሽን?»

«ምን ማለትህ ነው? እንዴት ይሆናል?»

« እና እኔን የምትወጂኝ ከሆነ የምልሽን ስሚ። በቃ ልጅ እንፈልጋለን ግን እግዚአብሔር አልሰጠንም። እሱ ፈቃዱ ሲሆን ይሰጠናል ወይም አይሰጠንም፤ በእጃችን ስላለ እንጂ ስለማንችለው ነገር መጨነቅ የለብንም። ፈጣሪ ካላለው አላለውም ነው። ሁለታችንም ተመርምረን መውለድ እንደምንችል ተነግሮናል። ከዚህ በላይ ምን ማድረግ እንችላለን?»

በንግግሩ የውስጧ ጥያቄ ባይመለስም ከዚህ በላይ አዝና ልታሳዝነው ስላልፈለገች እጆቹን በመያዝ መስማማቷ ገለጸች። ከሁሉም በላይ ደግሞ መታሰቢያን በጣም ስለምትወደው በዚህ ነገር ዳግመኛ ብታዝን እንኳ የተከፋች ላለመምሰል ለራሷ ማለች ተገዘተች።

በወሩ ሮሚ አረገዘች። ዘጠኝ ወራትና ጥቂት ቀናት ተደማምረው አልፈው እንሆ መውለጃዋ ተቃርቦ ሆስፒታል ተገኝታለች። የሚያዋልዳት ዶክተር ከሌላኛው ክፍል ጥቂት መሳሪያዎችን የያዘች ነርስ አስከትሎ ወደ ማዋለጃ ክፍሉ አመራ።

«ዶ/ር እባክህ ሚስቴ በኦፕራሲዮን ትውለድ። ጥሩ ስሜት አልተሰማኝም። በቃ የሚስፈልገውን ወጪ እሸፍናለሁ። እፈርማለሁም። በኦፕራሲዮን ትውለድ።» ዶክተሩን በሚለማመጡ አይኖቹ ተማጸነ።

«አቶ መታሰቢያ ወ/ሮ ሮሚ ደህና ሁኔታ ላይ ትገኛለች። ክትትሉ እንደሚያሳየውም ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ መውለድ ስለምትችል ኦፕራሲዮን ማድረግ አስፈላጊ አይደለም።»

«ግዴለህም ዶክተር በእኔ ይሁንብህ እኔ እዚህ ተጨንቄ ልሞት ነው። ሮሚም ብትሆን በምጥ ተዳክማለች እባክህ እሺ በለኝ።»

«ይኸውልህ አቶ መታሰቢያ እዚህ በስሜትና በመሰለኝ የሚሰራ ነገር የለም። የተለያዩ ሁኔታዎች ተጠንተውና ከግምት ገብተው ነው ስራ የሚሰራው እንዳልኩህ ወ/ሮ ሮሚን ኦፕራሲዮን እንድትሆን የሚያደርግ ምንም ዓይነት ሁኔታ አላየንም።»

ከዚህ በላይ መታሰቢያ ማውራትም ሆነ በውስጡ የተፈጠረውን ሁከት ማስረዳት አልቻለም። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሮሚ የተኛችበት ክፍል ተከፈተ። «አቶ መታሰቢያ» ስሙ ሲጠራ የሆነ የገደል ማሚቶ እንጂ የቅርብ አልመሰለውም። ተራሩጦ ገባ።

«ሮሚ ሮሚ የልቤ ንግስት።»

«መቲዬ... ሴት ልጅ ወለድኩ እኮ!» የደስታ እንባ በድካሟ ውስጥ ታየ።

«እንዴት ነሽ ሮሚ ደህና ነሽ?»

«ፍጹም ደክሞኛል.... ደስ ብሎኛል... መቲዬ ልጄ ማንን ትመስላለች?... አንተን ብትመስል ደስ ይለኛል።መቲ የለህም እንዴ!»

«አለሁ ሮሚ ....» ልጁን ለብቻ ወደ ተኛችበት አልጋ ሄዶ ተመለከታት። የሮሚን ገጽታ የሚመስል መልክ አስተዋለ። ደስ አለው። ወደ ሮሚ ሄዶ አልጋዋ አጠገብ በርከክ አለ።

«መቲዬ የልጃችንን ስም ፍቅር በልልኝ። የፍቅራችን መታሰቢያ ስለሆነች፤ ፍቅር መታሰቢያ በላት።» እጁን ጠበቅ ለቀቅ እያደረገች በተዳከመ ሁኔታ ንግግሯን ለመቀጠል ሞከረች።

«ሮሚዬ እየደከመሽ እኮ ነው ቆይ ሀኪም ልጥራ።»

«መቲዬ ስማኝ ቆይ በኋላ ትጠራቸዋለህ ወይም ሳትጠራቸው አሁን ይመጣሉ። ያልጠበቁት ደም መፍሰስ ስላጋጠመኝ ተቸግረው ከብዙ ድካም በኋላ መቆጣጠር የቻሉት የተለየ ነገር ከተሰማ ትጠራቸዋለህ። ይልቅ ስማኝ። ድንገት ያልጠበቅነው ነገር ቢሆን ልጄን አደራ።»

«ምን እያልሽ ነው?»

«ቆይቶ ይገባሃል። ልጄን አደራ ደግሞ እኔ አንተን አግብቼ ልጅ በቶሎ ስላልወለድኩ ደስታዬ ላይ ጥላ እንዳረፈበት ሁሉ ልጄም እናቷን የገፉች ተብላ ስትሳቀቅ መኖር የለባትም አደራው ለአንተ ነው።»

«ሮሚ እባክሽ እንደዚህ አትበይ።»

«አስጨርሰኝ ላይሆን ይችላል እኮ ከሆነ ማለቴ ነው።»

የሮሚ ድምጽ ቃናውን እያጣ እና ከስልት እየወጣ መጣ። መታሰቢያ ደስ አላለውም። ዶክተር ለመጥራት እጁን ከሮሚ እጅ አላቅቆ ከመሄዱ በፊት ሮሚ «መቲዬ እወድሃለሁ። ከአንተ ልጅ በመውለዴ ደስ ብሎኛል ልጃችን የፍቅራችን መታሰቢያ ናት። እንዳልኩት አሁን ብሞትም አይቆጨኝም.. መቲዬ እወድ...»ሀሳቡ አላለቀም ድምጿ እየተንሸራተተ መጥቶ በጸጥታ ተዋጠ። በሀይል ጮሆ ወጣ። «ዶክተር ... ነርስ ሚስቴን ፍቅሬን...» ጮኸ። ሁሉም ከያሉበት ተሯሩጠው ወደ ክፍሉ ገቡ። ሆኖም የሮሚ እስትንፋስ እየተቋረጠ ነበር።...

## መማር ማስተማሩን ...

ከገጽ 4 የዞረ

መደገፍ እና የምርምር ውጤቶችን ለማህበረሰቡ ተደራሽ በማድረግ የተገኙ ችግሮች እንዲፈቱ አቅጣጫ ለማሳየት በሚል አላማ እንደተዘጋጀ ገልጸዋል። በመሆኑም በአውደ ጥናቱ ላይ በዘርፍ የሚመለከታቸውን ውሳኔ ሰጪ አካላትና የማህበረሰብ ክፍሎች የተጋበዙ ሲሆን በአውደጥናቱ የቀረቡ የምርምር ሥራዎች በፕሮሲዲንግ በማሳተም ተደራሽ እንዲሆን ፋኩሊቲው እየሰራ ነው ብለዋል።

የአማራ ክልል ዩኒቨርሲቲዎች ፎረም ጽ/ቤት ዋና ፀሐፊ እና የሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ ተመራማሪ ፕሮፌሰር ዓብይ ይግባው መማር ማስተማሩ በምርምር መደገፍ የትምህርቱን ጥራቱ ለማስጠበቅና ተማሪው በእውቀት የበቃ ለማድረግ ወሳኝ ነው ብለዋል። ፕሮፌሰር ዓብይ አክለውም ፋኩልቲው ወደፊት በሚያዘጋጀው አውደጥናት «ጥራት ያለው ምርምር ለትምህርት ጥራት» በሚል መሪ ቃል ቢያዘጋጅ የሚል ሀሳብ ያቀረቡ ሲሆን ዩኒቨርሲቲዎች ለዩኒቨርሲቲዎች በአውደ ጥናት ብቻ ከመጠራራት ባለፈ በጋራ ተባብሮ ለመሥራት ስምምነቶችን በማድረግ የልምድ ልውውጥ ማድረግ እንደሚገባ ተናግረዋል።

በሁለቱ ቀን አውደ ጥናቱ ሀያ አንድ የምርምር ሥራዎች አስራ ሁለቱ የምርምር ሥራዎች በፋኩልቲው መምህራን የተሰሩ ናቸው። በቀረቡት የምርምር ሥራዎችም ላይ የተለያዩ ሀሳቦችና ጥያቄዎች ተነስተው ሰፊ ውይይት ተደርጎባቸዋል። በአውደ ጥናቱ ላይ የዘርፉ የውሳኔ አካላትና ተመራማሪዎች፣ ባለሙያዎች፣ መምህራን፣ የ2ኛና የ3ኛ ዲግሪ ተማሪዎች እና የፋኩልቲው ተመራቂ ተማሪዎች ተገኝተዋል።

# A Closer Look at Distance Education at BDU

By Yenus Nurie (Department of English Language and Literature)

The purpose of this paper is to send a sense of appreciation for what was done better and to forward a critical reflection on the possibilities of reforming distance education so that it provides a promising educational service to the public. Thus, this paper seeks not only to report about what has been achieved but also to figure out what were wrong and suggest the possible ways to avoid them.

Getting a university degree was a chimera for most of our people. However, thanks to civilization, we are observing people graduating from several universities in the country in many ways, such as regular, extension and summer. In addition, our university is known even promoting learning through the distance mode. Undoubtedly, this program is expected to provide access for those citizens who could not attend classes due to limited accommodation they encounter and for those who are unfortunate to learn by any means.

Despite its benefits of providing better opportunities and access to learning, distance education has shown little progress to achieve educational excellence as a result of which created disappointing outcomes on quality education. It has also challenged and embarrassed teachers. As a teacher, I was incredibly nervous about the disorganized practices of distance education unit in the last couples of years. Frankly speaking, it upset me like one of the hardest parts of my life. Hence, as a distance education tutor, invigilator and exam paper corrector for the last few years, I think, it is my moral duty to reflect on the ongoing efforts of our distance education program and thereby address concerns that can deter the overall goals of the program.

To begin with, I was certainly impressed more than ever since I knew distance education program, for I observed some new wonderful practices that could demonstrate a glimmer of hope in improving the efficiency of distance education. Although small in scale and still the program is at its infancy, I was able to observe a little progress that should be appreciated. Besides launching the SIMS that has turned out to be successful like regular students, distance education has made a huge progress in structuring exam rooms to contain as small students as possible. I saw the zeal and commitment of the coordinators and its staff to accomplish exam sessions successfully, and this interested me. Thinking that the distance program made strong orientation to examinees to arrive earlier than usual, I observed little or no disruption of the exam sessions. On top of this, the effort made by the program to reach out the learners by providing transport services before and after the exam was unusual for me and, I think, the program deserves more appreciation.

Nevertheless, even with the minor problems I do not wish to pursue, I saw some examinations that were not well-edited and proof-read. For example, some exam questions seemed to lack clear instructions, and still others require revision as it was possible to get a question repeated two or more times in the examination. The other disgusting and unprofessional act that embarrassed me was that I found very few invigilators who left examinees alone while they were seen sitting somewhere far from controlling properly. In other words, incoherent examinations procedures were held as finding some invigilators sitting aside somewhere in the class which strict control was found to be pointless.

Apart from this, I hear teachers here and there blaming the unit, for the slow disbursement which they were unable to secure their overtime payment even after three months they accomplished their tasks. This recent trend must be revisited as it is contrary to the law which requires employers to pay their employees in a timely manner. It is also a fundamental cause for customers' dissatisfaction.

In brief, to sustain what has been attained and fix the serious concerns mentioned above, I suggest that distance education should set up two sub-units under the supervision of the program. First, the program should be committed to establishing invigilator evaluation mechanisms like the one that the program had started assessing its tutorial sessions a year ago although I haven't seen any since then. It also needs to set up exam coordinating and supervising units that ensure the efficiency and quality of examinations. By doing so, I hope the program will get a better sense of examining students in more accountable ways in the future. On the whole, customers as well as the university will be grateful if the glimmers of hope that we are observing in recent months are further strengthened by acknowledging what has been done and finding urgent solutions to examination and invigilator malpractices.

# Save the Oxen for Your Survival

Chalachew Tarekegne (PhD Candidate)
Department of Civics and Ethical Studies

The beginning of agriculture was a revolutionary development in early Africa. Gradually, it led to greater economic, social and political changes. In the era of the Stone Age, Africans had lived by hunting wild animals and by gathering plant foods such as berries, seeds, and roots. People who lived near lakes and rivers fished for much of their food. The hunters and gatherers lived in small groups. As the seasons changed, the groups could thus move easily from place to place to follow the migrations of animals and to search for plant foods. But, after people learned how to grow crops, tame and raise animals, they no longer had to move about to get food. They could then establish permanent settlements.

Agriculture spread in Africa over thousands of years ago although no one knows for certain when or where it began on the continent. In parts of Africa, agriculture probably was introduced by people who had migrated from other places. In some other areas, the people may have experimented with native wild grasses and eventually figured out how to grow the grasses as cultivated grains. Many experts believe that farming began in the Middle East and then spread westward into northern Africa. *Some experts believe that Africans in other areas, including the present day Ethiopia and Kenya, may have developed agriculture on their own even earlier.* (***Source**: The World Book Encyclopaedia: 1994).*

Let's ponder over the matter. It seems sensible to hypothesise that agriculture is native to Ethiopia, and hence we have had thousands of years farming experiences. But, it is to be regretted that almost 95% of the smallholder farmers in Ethiopia are still using primitive way of farming which forced them lead their lives below the poverty line. Though there are efforts made by both federal and regional governments to solve the problems and help each farmer benefit from agricultural research findings and innovative farming approaches, many more farmers are still suffering from food insecurity and remain vulnerable to different diseases and pestilences. Thus, confronting this still needs lot of endeavours from the research community of Ethiopia in general and regional satellites in particular.

Due to large number of deeply ingrained problems in the sector, it would be impractical to think that government can alleviate all the problems by itself alone. Researchers who are competent in producing articles in reputable international journals in the field should enthusiastically maximize their full potential by innovating new technology to replace the very traditional farming methods. Government, researchers, and farmers have to create merit-based alliance to maximize productivity through proper applications of modern farming methods by merging it through the capabilities of indigenous wisdoms. Unlike the present trends, we should not only encourage farmers to take part on the extension packages to increase productivity but also teach advise and train them to be Agriculture Smart Professionals.

It is important to note that the dependency on foreign aid for the last fifty years to modernize our agriculture has not always been beneficial for the poor helpless farmers of Ethiopia. Hence, researchers who aspire to build "Basket Bread Ethiopia" must devote their effort until they achieve their goals. It is a well-known fact that aid projects except some of them are rarely contributing for the national goal of the country. Surprisingly, many of these aid projects made the people develop dependency. Worst of all, since many loans call for high interest payments, donor countries end up with more financial benefits than the receiving countries like Ethiopia.

The aim of this piece of personal reflection is not to provide evidence about the ancient lineage of agriculture to *Greater Abyssinia*, but to examine one of the future challenges of Ethiopian agriculture in the coming thirty-fifty years. In fact, national policy makers have given due recognition to the prevailing effects of the following mega trends: population pressure, climate change, food insecurity, natural resources depletion; and overall, bio-system disintegration, yet lots of endeavours are still needed to solve problems associated with them.

The tragedy now is that Ethiopian oxen are swiftly disappearing from our lives. The core purpose of this piece of reflection is; therefore, to exhort people to give due consideration on the survival of the engines of Ethiopian Agriculture-Oxen. Indeed, Ethiopians are proud of having oxen, for they are credited for our success. Thus, I contend that

continued on page 10

# “ነፃ አውጪው” ማን ነው?
# ቅኝ ገዢ፣ ነፃ አውጪ መሆን ይቻለዋልን?

ከባለፈው ወር እትም የቀጠለ

ጀማል ሙሀመድ ሀይሌ (ዶ/ር)
ከጋዜጠኝነትና ስነተግባቦት ትምህርት ክፍል
jemalmohammed99@gmail.com

## ቅኝ ገዥ

ጫት - እንደ ማንኛውም ሱስ አስያዥ እፅ - አንድ ሰው ሲቅመው መጀመሪያ ላይ ድብርትን የማስወገድና የማነቃቃት ባህሪ አለው፤ ተጠቃሚው ሰውዬ ቂምሀውን እየጨመረ በሄደ ቁጥር መነቃቃቱ እያደገ-እያደገ ይሄድና ይመረቅናል፤ ሰውዬው ምርቃናው ከደረሰበት ደረጃ ላይ መቆየት ይፈልጋል - ደስ-ደስ የሚል ስሜት ያለው ከምርቃናው ጣሪያ ላይ ነውና፡፡ በዚህ ስሜት ውስጥ ለመቆየት ሲልም አነሰም-አደገም ጨመርመር አድርጎ መቃም አለበት፡፡ አለበለዚያ ምርቃናው ይቀለበሳል፤ የምርቃና መቀልበስ ደስ የማይልን ስሜት በመፍጠር ብስጭትን፣ መነጫነጭን፣ ወዘተ. ያስከትላልና አይፈለግም፡፡ ተጨማሪ መቃም በበኩሉ ምርቃናውን ሰውዬው ሊሸከመው ከሚችለው በላይ ያደርገውና - ማለትም ያሰክረውና - ከድብርት አዚም ውስጥ ይከተዋል፡፡ እናም በዚያም አለ በዚህ ጫት ከቃሙ በኋላ ድብርት ወይም መፍዘዝና መደንዘዝ የማይቀር ውጤት ነው፡፡ (አንዳንድ ቃሚዎች ይህን ስሜት ለማስወገድ በማሰብ ነው፡፡ ወደ ጨብሲ የሚሄዱት፤ ሆኖም ነገሩ ከእንጨት ክምር ላይ የተቀጣጠለን እሳት በነዳጅ ለማጥፋት የመሞከር አይነት ትግል ነው፡፡)

ቂምሀው እየተዘወተረ በሄደ ቁጥር ደግሞ የቂምሀው አስፈላጊነት ወይም ግድነት እየጨመረ ይመጣል፡፡ እናም ሰውዬው መደበኛ ቃሚ ከመሆን ይደርሳል - በቀን ቢያንስ አንድ ጊዜ (ቀን ወይም ማታ) የሚቅም፡፡ የባህር ዳር ጫት በባሕር ዳር ቃሚዎች ላይ ከዚህ የተለየ ያደረገው ነገር የለም፡፡ በተግባር እያየነው ያለው ሀቅ ይሄው ነው፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ ብዙ ቃሚዎችን፣ ብዙ ቃሚዎችን ብቻ ሳይሆን ብዙ ሱሰኞችን፣ ብዙ ሱሰኞችን ብቻ ሳይሆን ብዙ ተጎጂዎችን እያፈራ ነው ያለው፡፡ ብዙ፣ እጅግ ብዙ ሰዎችን የሱስ እስረኛ አድርጎ፣ ከሱስ ወህኒ ቤት አጉሯል፡፡ ብዙ፣ እጅግ ብዙ ሰዎችን የሱስ እስረኛ አድርጎ፣ ከሱስ የባርነት ሸለቆ ቀብሯል፡፡ ታዲያ ይህ ሁሉ ድርጊት የቅኝ ገዥ እንጂ እንደምን የነፃ አውጪ ተግባር ሊሆን ይችላል? አሁንም እጠይቃለሁ - ቅኝ ገዥ ነፃ አውጪ መሆን ይቻለዋልን?

የባህር ዳር ጫት ለባሕር ዳር ቃሚዎች ቅኝ ገዢያቸው ነው፤ እንደ ፍልስጤሞች መቼ ነፃ እንደሚወጡ በማያውቁት ሁኔታ ውስጥ ያሉ የጫት ቅኝ ተገዢዎች ናቸው፡፡ “ከዛሬ በኋላ ‘ጫት’ እሚባል ቅጠል ባፌ አይዞርም” በማለት ቁርጠኛ አቋም በመውሰድ ያቆሙት ብቻ ናቸው ነፃ አውጪዎች - ራሳቸውን ከጫት የጭቆና ቀንበር ነፃ ያወጡ አርበኞች፡፡ ከጫት የቅኝ ግዛት ቀንበር ስር ወድቀው የሚማቅቁትን ሰዎች፣ ከጫት የሱስ ባርነት እንዲላቀቁ የሚያስተምሩት ናቸው ነፃ አውጪዎች፡፡ ከነዚህ ውጭ ያሉት ቃሚዎች በሙሉ የጫትን የጭቆና ቀንበር ወደው የተሸከሙ፣ ራሳቸውን ነፃ ማውጣት እንደሚችሉ ተስፋ የቆረጡ፣ የጫት ቅኝ ተገዢዎች ናቸው፡፡ እናም የባህር ዳር ጫት “ነፃ አውጪያቸው” ሳይሆን፣ ቅኝ ገዢያቸው ነው፡፡ መዳብን ወርቅ፣ ዳጉሳን ጤፍ ቢሉት ጥቅም የለውም - ራስን ከማታለል ውጭ፡፡

ባጭሩ የባህር ዳር ጫት ከትውልድ ቦታው ከባህር ዳር ላይ ነፃ አውጪ አይደለም፡፡ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ከጊዜ ወደ ጊዜ ስርጭቱን እያሰፋ ነው ያለውና፤ እግሩን በዘረጋባቸው፣ እጁን በሰደደባቸው ከባህር ዳር ውጭ ባሉ ከተሞችስ ምን አይነት ሚና ይኖረው ይሆን? ምናልባትም፣ “ጅብ ከማያውቁት አገር ሄዶ፣ ‘ቆዳ አንጥፉልኝ አለ’ ” እንዲሉ፣ ከባህር ዳር ውጭ ያሉ ቃሚዎችን፣ በተለይም ምርቅንቅን ያሉበትን ቅፅበት ጠብቆ፣ “ቆንጂዬ ስም አውጡልኝ” ብሎ

> ነገ-ከነገ ወዲያ
> ብዙዎቹን የሀገሪቱን ከተሞች እንደማያዳርስ ማረጋገጫ የለንም፤ ብዙዎቹን የሀገሪቱን ቃሚዎች “ነፃ እንደማያወጣ” ሳይሆን ከቅኝ ግዛቱ ስር እንደማያውል እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡

ጠይቋቸው ይሆን “ነፃ አውጪ” በማለት ያንቆላጰሱት - ነገሩ “እነመልከ ጥፉ፣ በስም ይደገፉ” ቢሆንም? ለማንኛውም የባህር ዳር ጫት “ነፃ አውጪ” የመባሉ ጉዳይ እንደ አክሲዮን ስያሜ በሁሉም ቃሚዎቹ (ከባህር ዳር ውስጥና ውጭ ባሉት) በጋራ ይሁንታ የወጣ ባይሆንም ከባሕር ዳር ውጭ ያሉት ቃሚዎችም ባለድርሻ አካላት ናቸውና በነሱ በኩል ያለውን ሁኔታ ትንሽ ፈተሽ ማድረጉ አይከፋም…

ከሶስት አመት በፊት ጥር ወይም የካቲት ወር አካባቢ ላይ ወደ ትውልድ ቦታዬ - ደሴ - ሄድኩ፡፡ በነጋታው ከሰአት በኋላ አካባቢ ተወልጄ ወደ አደኩበት ሰፈሬ አመራሁ - ደረቱን እንደ ነፋ ግርማ ሞገስ የተላበሰውንና ርቀውት በሄዱ ቁጥር ልብን በናፍቆት ማእበል የሚሞላውን የጦሳ ተራራን ተደግፎ ወደሚገኘው ዳውዶ ወደሚባለው ሰፈሬ፡፡ በእድሜ ትንሽ የምበልጠውን አብሮ አደጌን ሰይድን ላየው ወደ ሱቁ አመራሁ፡፡ ሰላምታ ተለዋወጥን፡፡ ወቅቱ ከሰአት በኋላ ቢሆንም እንደ ወትሮው ጫት እየቃመ አላገኘሁትም፡፡ ያልተለመደ ነገር ስለገጠመኝና ጫት መቃም ያቆመ ስለመሰለኝ፣ “ማሺ አሏህ!” (“አሏህ የፈቀደው ሆነ”) አልኩ፡፡

“ለምኑ ነው ‘ማሺ አሏህ’ ያልከው” አለኝ፡፡
“ጫት መቃም ስለተውክ” አልኩት፡፡
“አይ ጀማል! ትቸ መሰለህ? አይደለም፡፡”
“ታዲያ ምክንያቱ ምንድነው?”
“ጫት በዚህ ሰአት ደሴ ውስጥ ዋጋው ሰማይ ነው፡፡ በትንሹ በቀን ሶስት መቶ ብር ያላወጣ ሰው ጋሌሳን (ሀይቅ ከሚባለው አካባቢ የሚመረት የጫት አይነት ነው) መቃም አይችልም፡፡ በቀን ሶስት መቶ ብር አውጥተን ምን ልንበላ ነው?”
“ይህን ያህል ይወደዳል?” በማለት ጠየኩት፡፡
“አዎ - የናንተ ጫት ባይኖር ኖሮ የደሴ ሰው የት እንደሚደርስ አላቅም፡፡”
“የናንተ ጫት ስትል?”
“የባሕር ዳር ጫት! እሱ ነው እዚህ ብዙውን ቃሚ ቀጥ አድርጎ የያዘው” ብሎኝ እርፍ… ልንለያይ መሰነባበት ስንጀምር፣ “ይሄው አሁን ጫት እየቃምክ አይደለም፡፡ ይህ ማለት የጫት ሱስ አያስቸግርህም ማለት ነው፡፡ ለምን መቃሙን አትተወውም?” አልኩት - ሰይድን፡፡
በፈገግታ ተሞልቶ፣ “ኢንሻ አሏህ (የአሏህ ፈቃዱ ከሆነ)” በማለት ተስፋ ሰጠኝ…

በጋዜጠኝነት ሙያ ስሰራ በነበረበት ወቅት ከሶስት የስራ ባልደረቦቼ ጋር ወደ እንጅባራ ከተማ ለመስክ ስራ ሄድን፡፡ አንድ ቀን የዘገባ ስራችንን ስንከውን ቀኑን አጋመስንና ምሳችንን በላን፡፡ አንዱ ባልደረባችን ጫት ሊገዛ ሄደ፡፡ ጫት አልመጣም፡፡ ጫት ሳይቅም መዋል ደግሞ አይችልም፤ ሀራራው ያሰቃየዋል፤ ይህ የቀን ስቃይ ነው፡፡ ማታ ሲተኛ ደግሞ ከዚህ የከፋ ስቃይ ይጠብቀዋል ወይም እንደሚያጋጥመው ይጠብቃል…

ብዙዎቹ “መደበኛ” ቃሚዎች እንደሚናገሩት ጫት ሳይቅሙ ከዋሉ ማታ ሲተኙ ዱካክ ያሰቃያቸዋል፡፡ እነሱ እንደሚሉት ከሆነ፣ ዱካኩ ከቃሚው የራስ ፀጉር መካከል አንዷን ብቻ በመያዝ ቃሚውን ወደ ላይ ካንጠለጠለው በኋላ ወደ ገደል ጫፍ ይወስደዋል፡፡ ከገደሉ አፋፍ ላይ በመቆም፣ በዚያቹ በአንድ የራሱ ፀጉር ከገደሉ ላይ እያንጠለጠለው፣ “ዛሬ ለምን አልቃምክም፤ አሁን በዚህ ገደል ልልቀቅህ” በማለት ያስጨንቀዋል… ወይም ደግሞ ከላዩ ላይ እንደ ዝሆን ከሰፈረበት በኋላ፣ “ዛሬ ለምን አልቃምክም?” ይለዋል፡፡ “ጫት አጥቼ” ካለ፣ የአንድ አህያ ጭነት ሊሆን የሚችል ገረባ (የደረቀ የጫት እንጨት) ያመጣና እያነሳ ከአፉ ውስጥ ሲከትበት፣ ሲጠቀጥቅበት ያድራል፤ ጉንጮቹ እየተበሱና በደም እየራሱ ስቃዩን ሲበላ ያድራል፤ ወይም ጮሆ በመባተት ከስቃዩ ይገላገላል… ወይም ደግሞ ዱካኩ የራሱን ጫት ይዞ ሊመጣ ይችላል፡፡ እናስ - “ ‘ጀለሴ፣ ና አብረን እንቃም’ ሊለው?” በምን እድሉ! ዱካኩ፣ ጫት ያልቃመውን “ደንበኛ” ከንፈር ዳርና ዳሩን በመያዝ፣ ወደ ጎን ይለጥጠዋል፤ ለጥጦ-ለጥጦ በጣም ጠባብ ሊባል የሚችል የአልቤርጎ ክፍል ያህል ያሰፋዋል - አፉን… አቤት ስቃዩ! ከዚያ ምንጣፉን ከአፉ ውስጥ ያነጥፋል፡፡ ከዚያ ከአፉ ውስጥ ይገባል፤ ጫማዎቹን በማውለቅ፣ ከከንፈሩ ላይ ያስቀምጣል፤ ከምንጣፉ ላይ ቁጭ ይልና ጫቱን መቃም ይጀምራል… አቤት ክብደቱ፣ አቤት ስቃዩ!… እንደ ገና ይወጣና የተቀጣጠለ ከሰል የያዘ ማጨሻ ያመጣል፡፡ ከነማጨሻው ከአፉ ውስጥ ይገባል፤ ከሰሉን ያራግበዋል፤ አቤት ጭሱ፣ አቤት ግለቱ… “አሁን-ካሁን አንድ ፍም ከአፌ ላይ ወደቀ፣ ከምላሴ ላይ አረፈ”… እናም ይህን ሁሉ የስቃይ ክምር ላለመሸከም ለመደበኛ ቃሚዎች የተገኘውን መቃም አማራጭ የለውም…

በነገራችን ላይ ዱካክ ምንድነው ወይስ ማን ነው? ቃሚዎች በአእምሯቸው ራሳቸው ስለሳሉት ሳይቅሙ ሲቀር አእምሯቸው ስለሚጠብቀው ከተፍ እያለ የሚጋልባቸው የጭንቀት ትርኢት? ወይስ ከጫት ሱስ ጋር የተያያዘ ሰይጣናዊ መንፈስ?… የሙያው ባለቤቶች በጥናታቸው ቢፈትሹት…

እንጅባራ ለመስክ ስራ አብሮን የሄደው ባልደረባችን፣ ዱካክን ለመሸሽ ሶስት ወይም ሁለት ቀን ያደረ ጫት ወደ አረፍንበት ቤርጎ ይዞ መጣ፡፡ ያለ ምንም ማጋነን፣ አብዛኛዎቹ የጫት ቅጠሎች ወይ ከጫፋቸው ወይም እስከ ግማሽ ወገባቸው ወይ ወይበዋል ወይም ደርቀዋል፡፡ የወየበና የደረቀውን እየበጠሰ እየጣለ፤ አረንጓዴ፣ አረንጓዴዋን የጫት ቅጠል እየቀነጠበና እየለቀ ሲቅም አስታወሳለሁ… ከተወሰ አመት በኋላ ስራውን ለቆ አዲስ አበባ ገባ…

ከሁለት አመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አዲስ አበባ ተገናኘን፡፡ ወደ ቤቱ ወስዶ ጥሩ ምሳ ጋበዘኝ፡፡ የጫት ታሪኩን አወራን፡፡ አሁን በሳምንት አንድ ጊዜ (ቅዳሜ) ብቻ ነው የሚቅመው፡፡ ለምን? “የበለጬን (ያዲሳባን ጫት) ዋጋ ማን ችሎት?” አለኝ፡፡ የባህር ዳር ጫት ሰውን በጫት ሱስ ለማስለከፍ ወደር

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# እንግዳችን

## በፍላጎቶች ግጭት ተጠላልፈን ስለምንገኝ ችግር ፈቺ ትምህርትንና ተቋማዊ ሥርዓትን በሚመሳስሉ ታላላቅ እሳቤዎች ላይ የጋራ መግባባት ለመድረስ እጅግ እንደ ከበደን እንገኛለን፡፡

**ዶ/ር መስከረም ለቺሳ**

የዚህ ወር እንግዳችን በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ትምህርትና ስነ-ባሕርይ ኮሌጅ ረዳት ፕሮፌሰር ናቸው፡፡ የህይወትና የስራ ተሞክሯቸውን አስመልክቶ ከናይል ጋዜጣ ጋር ቆይታ አድርገዋል፡፡ ቃለ መጠይቁን እነሆ፡፡ መልካም ንባብ!

**ናይል፡-** በቅድሚያ ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ በመሆንዎ በናይል ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ስም እያመሰገንን ሙሉ ስምዎትንና የሥራ ኃላፊነትዎን ቢያስተዋውቁን?

**ዶ/ር መስከረም፡-** ስሜ መስከረም ለቺሣ ይባላል፡፡ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በትምህርትና ስነ-ባሕርይ ኮሌጅ ረዳት ፕሮፌሰር ነኝ፡፡ የዩኒቨርስቲው የአቅም ግንባታ መርኃ-ግብር ማዕከል ም/ዳይሬክተር ነኝ፡፡

**ናይል፡-** ስለ ትውልድ ቦታዎ እና የተማሪነት ህይዎትዎ ቢያጫውቱን?

**ዶ/ር መስከረም፡-** የተወለድኩት ሐረር ከተማ ነው፤ በ1977 ዓ.ም.፡፡ የተማሪነት ሕይወቴ ሁለት ዓይነት መልክ አለው፡፡ አንደኛው በትምህርቴ በኩል ጥሩ ውጤት እንዳስመዘግብ ከቤተሰቦቼ ክትትል ይደረግልኝ ስለነበረና በቤት ውስጥም እኔም ሆንኩ እኅቶቼና ወንድሞቼ ደስተኞችና ንቁዎች ሆነን እንድናድግ ወላጆቼ ከፍተኛ መስዋዕትነት በመክፈል ይንከባከቡን ስለነበር በነጻነት የማሰብንና የትምህርትን ፍቅር ይዘን ለማደግ ዕድሉን እንድናገኝ የሆንበት ገጽታ ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን በቀጡ 5 ዓመት እንኳ ሳይሞላኝ አንደኛ ክፍል ስለገባሁና በዚያም ላይ ከክፍል ክፍል የተዛወርኩበት ሂደት የተፋጠነበት አጋጣሚ ስለተከሰተ ከክፍል ጓደኞቼ ጋር በዕድሜ እኩያነት የተራመድኩበት ጊዜ አለመኖሩ የፈጠረው ትንሽ ክብደት ነበረ፡፡ ሆኖም ፈረንጆቹ “blessing in disguise” እንደሚሉት ይህ ክፍተት ብዙ ጉዳት ሊኖራቸው ይችሉ የነበሩ ነገሮችን ብዙም ሳላስተውላቸውና ሳይይዙኝ በጊዜ ትምህርት ቤትን እንድጨርስና ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም እንድንገባ ረድተውኛል፡፡

**ናይል፡-** ስለ ግል ህይወተዎ እና የትዳር ሁኔታዎ ቢያጫውቱን?

**ዶ/ር መስከረም፡-** ከባለቤቴ ጋር የተገናኘነው እዚሁ ባሕር ዳር ነው፡፡ የመጀመሪያ ዲግሪዬን ከጨረስኩ በኋላ እኔ በዚያኔው የትምህርት ፋኩሊቲ እርሱ ደግሞ በኢንጂነሪንግ ፋኩሊቲ ረዳት ምሩቆች ነበርን፡፡ ጋብቻችንን በ1998 ዓ.ም. ፈጽመን፡፡ እኔ ወዲያውኑ ወደ አሜሪካ ስሄድ እርሱ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሁለተኛ ዲግሪውን እየሠራ ነበር፡፡ እንደ ጨረሰ ወደ አሜሪካ መጣና በዓመቱ ሦስተኛ ዲግሪውን መሥራት ጀመረ፤ እኔም ተከተልኩት፡፡ እንግዲህ ጎጆ የወጣነው በምድረ-አሜሪካ ነበረ ማለት ነው፡፡ ታድያ ባለቤቴ ነገረ ሥራዬ ሁሉ የጀብደኝነት ወይም የብስለት ማጣት ችግር እየመሰለው ነው መሰለኝ ፈጽሞ በቀና የሚያየው ነገር ጠፍቶ በመካከላችን ለረዥም ጊዜ አለመግባባት ሰፍኖ ነበር፡፡ እኔ እያለፍኩ የነበረበት ችግር ከእኔ አቅጣጫ ሊታየው ፈጽሞ አልቻለም፡፡ ያም እያደገ መጥቶ ትዳሩ በራሱ በእኔ ላይ በግል የተፈጸመ ሴራ እስኪ መስለኝ ድረስ ብዙ ተስፋ የሚያስቆርጡኝ ነገሮች ተከስተው ነበር፡፡ እያደር ደግሞ ባለቤቴ የነበረው አስተሳሰብ ስህተት መኾኑን ሲረዳ ለተፈጠረው ክፍተት ኃላፊነት ለመውሰድ ስለከበደው እንደ አማራጭ አድርጎ የወሰደው የበለጠ ራሱን ማግለል ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ወደ አገር ቤት ስንመለስ በቀጥታ ጋብቻው እንዲፈርስልኝ በመጠየቅ ነበር ኑሮዬን የጀመርኩት፡፡ ሆኖም ፊርማው ሊቀደድ አንድ የፍርድ ቤት ቀጠሮ ብቻ ሲቀረው ፈጣሪ በአንድ ቅን ሰው ላይ አድሮ (አሁን ነዋሪነቱ በአዲስ አበባ ነው) ባለቤቴ ጥፋቱን ለማመን እንዲደፍር በትዕግሥት ሲያስረዳውና ሲወቅሰው ብዙ ቀናትን ቆይተው በስተመጨረሻ እውነተኛ ይቅርታ ለመጠያየቅ ስለበቃን ሊቆረጥ የነበረው ተቀጥሎ አሁን በአንድ ላይ ነን፡፡ እኔና ባለቤቴ በፈለግነው ርእሰ ጉዳይ ላይ እንደልብ የምናወራ ጥሩ ጓደኛሞች ከመኾናችን በተጨማሪ አፈጣጠራችን ራሱ የአንዳችን ደካማ ጎን ኹሉ የሌላችን ጠንካራ ጎን ኾኖ የሚገኝበት ሆኑ ብንለያይ ለኹለታችንም ትልቅ ጉዳት ይኾን ነበር፡፡ በዚህ ሁሉ ሂደት ውስጥ “ትዳር የሚፈርሰው ለካ ቅን ሽማግሌ ከማጣት ነው” ብዬ እስካምን ድረስ ብዙ ነገሮችን ተመልክቼበታለሁ፡፡

**ናይል፡-** የመጀመሪያ፣ የሁለተኛና ሶስተኛ ዲግሪዎትን በምን በምን የትምህርት ዘርፍ አገኙ?

**ዶ/ር መስከረም፡-** የመጀመሪያ ዲግሪዬን ያገኘሁት እዚሁ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ነው፡፡ በ1996 ዓ.ም. በፔዳጎጂካል ሳይንስ እና በጂኦግራፊ (“composite major” ይባል በነበረው) የዲግሪ መርሓግብር ነበር የተመረቅሁት፡፡ ሁለተኛ ዲግሪዬን አሜሪካን አገር በአዮዋስቴት ውስጥ በሚገኘው የሰሜን አዮዋ ዩኒቨርስቲ በEducational Psychology አግኝቼያለሁ በ2000 ዓ.ም. ማለት ነው፡፡ ሦስተኛ ዲግሪዬን ደግሞ በ2006ዓ.ም. ማብቂያ በዚያው በአሜሪካ በኦሃዮ ግዛት በሚገኘው በሲንሲናቲ ዩኒቨርስቲ በCurriculum and Instruction ዘርፍ አግኝቼያለሁ፡፡



**ናይል፡-** በውጭ ሀገር የሥራ ቆይታዎ ያገኙትን መልካም ተሞክሮ ቢያካፍሉን? ስኬታማ ነበር ብለው ያምናሉ?

**ዶ/ር መስከረም፡-** በውጭ አገር የነበርኩት በትምህርት ላይ ነበር፡፡ ሥራ እየሠራሁ የነበረው በዚያው በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ በረዳት ምሩቅነት (graduate assistantship) ነበር፡፡ ለምሳሌ፡- አዮዋ ሁለተኛ ዲግሪዬን እየሠራሁ በነበርኩበት ጊዜ በአንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ የሂሳብ ትምህርት በአገር-አቀፍ ደረጃ ታዋቂ ባለሙያ ከነበረች ኤላናጆራም ከምትባል ፕሮፌሰር ጋር ለመሥራት ዕድሉ ገጥሞኛል፡፡ ዶ/ር ጆራም ጥናትና ምርምርን የሃይማኖት ያኽል በጥንቃቄ የምትሠራና ከፍተኛ ግምት የምትሰጥ ምሑር ናት፡፡ እርሷ በምትሠራቸው ምርምሮች ውስጥ በመረጃ ትንተና (data analysis) አግዛት ነበር፡፡ ከርሷ ብዙ ነገሮችን ተምሬያለሁ፡፡ በተጨማሪም ራድሂአል-ማቡክ ከሚባል የሥነ-ልቦና ባለሙያ እና ጆንሄኒንግ ከሚባል አማካሪዬ ጋር ለአጫጭር ጊዜዎች በመረጃ ትንተናና ተያያዥ የምርምር ሥራዎች ሠርቼያለሁ፡፡ ሦስተኛ ዲግሪዬን እሠራ በነበረበት ወቅትም እንዲሁ በነበርኩበት የትምህርት ክፍል ለሁለት ዓመታት በረዳት ምሩቅነት ሠርቼያለሁ፡፡ለምሳሌ፡- ሦስተኛ ዓመት ቅድመ-ምረቃ መምህራን ለልምምድ ወደ ትምህርት ቤቶች ከመውጣታቸው በፊት Micro-teaching የሚባል በመቅረጸ-ምስል (Video) የሚቀረጽ የማስተማር ልምምድ የሚሠሩበትን መርሐ-ግብር በመከታተል ማስፈጸምና ምን ማሻሻል እንዳለባቸው አስተያየት መስጠት አንዱ የሥራ ድርሻዬ ነበር፡፡ ከሁለተኛ ዲግሪ መርሃ-ግብር ጋር አብሮ የሚሰጥ የመምህርነት ሙያ ማረጋገጫ የሰርተፊኬት መርኃ-ግብር (Masters plus licensure program) አዲስ ገቢዎችን ስለመርኃ-ግብሩ መረጃ መስጠትና ያላቸውን ጥያቄ መመለስ ሌላኛው የሥራ ድርሻዬ ነበር፡፡ በተጨማሪም አዲስ ተመራቂ ነጮች መምህራን ጥቁሮች፣ ላቲኖችና ሌሎች መጤዎች በሚበዙባቸው ትምህርት ቤቶች እንዲያስተምሩ ሲመደቡ በብዛት በደስተኝነት ስለማይቀበሉት የአስተሳሰብ ለውጥ የሚያገኙበትን ሴሚናር በማካኼድ ለአጭር ጊዜ ሠርቻለሁ፡፡ ከጉዳዩ ውስብስብነትና በተማሪዎችም ዘንድ ስሜታዊነትን የሚያመጣ ከመኾኑ የተነሳ ሥራውን ወዲያውኑ እንድቀይር አመልክቼ ብለውጥም በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ነገሮችን የተረዳሁበትና አሜሪካን ላይ ላዩን ሳይሆን በደንብ እንድረዳት ዕድል የሰጠኝ ወርቃማ አጋጣሚ ነበር፡፡ ከዚያ ውጭ በኦሃዮ ለአዲስ የሁለተኛ ደረጃ የማኅበራዊ ሳይንስ ሥርዓተ ትምህርት ትግበራ ይደረጉ በነበሩ ቅድመ-ጥናቶች ላይ በረዳትነት ተሳትፌያለሁ፡፡ ይህ ሁሉ በኮርሶች ከሚገኝ እውቀት በበለጠ እጅግ ብዙ

⇨

# እንግዳችን ...

ልምድ እንዳገኝ ረድቶኛል። በምዕራቡ ዓለም በትምህርቱ ዘርፍ ያሉ ወቅታዊ ጉዳዮችንና ተግዳሮቶችን በሚገባ ተረድቼበታለሁ። በዚህም የሥራ ልምዴ ስኬታማ ነበር ለማለት እችላለሁ።

**ናይል፡-** **ለተማሪው ተሳትፎ ትኩረት የሰጠ፣ ተግባር ተኮር የሆነ፣ የሃገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ፣ በነፃ ማሰብ የሚያበረታታ፣ ዘመናዊ አመለካከቶች የሚያንፀባርቅና ችግር ፈች የሆነ ዜጋ ማምረት የሚችል ተቋም እንዴት መፍጠር ይቻላል? ከውጭ ተሞክሮዎ ቢያካፍሉን።**

*ዶ/ር መስከረም፡-* ችግር ፈቺ የሆነ ትምህርትና ተቋማዊ ሥርዓትን መፍጠር ይቻላል አይቻልም ብለን ለማመን የሚያበቃን ምንም ምክንያት የለም። "አይቻልም" ብሎ መደምደምም ጤናማ አቋም አይደለም። እኔ "ይቻል ይኾን?" ከሚለው ጥያቄ ይልቅ "እንፈልጋለን ወይ?" ብለን ብንጠይቅ የተሻለ ይመስለኛል። ለዚያ ምላሻችን "አዎ" ከሆነም ቀጣዩ ተገቢ ጥያቄ "የማንን እና የቱን ችግር ነው በቅድሚያ ልንፈታ የምናስበው?" የሚለው ነው። እኔ ችግር ፈቺ የሆነ ትምህርትም ሆነ ተቋማዊ ሥርዓት የሚመጡት ይህን ጥያቄ በግልጽ ከመለስንና የጋራ መግባባት ላይ ከደረስን ብቻ ነው ብዬ አምናለሁ። ምክንያቱም አንዱ "ይህ ነገር ችግር ነው፤ ተባብረን ልናስወግደው ይገባናል" ብሎ የሚያስበውን ክስተት ሌላው "ይህ ጥሩ አጋጣሚ ነው። አንድ ማኅበረሰብ ሊያልፍበት የሚገባ ተፈጥሯዊ ሂደት ነው" ብሎ የሚያምን ከኾነ ችግር-ፈቺ መሆን የሚባል የሚያግባባን የትምህርት ሥርዓት ሊኖር አይችልም። ምክንያቱም ችግሩ ላይ ራሱ አልተስማማንምና።

ለምሳሌ ብዙ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ሕጋዊም ይሁን ሕገ–ወጥ በሆነ መንገድ ከአገር ውጭ በአራቱም አቅጣጫ የሚሰደዱበትን ሂደት አንዱ ተስፋ የመቍረጥ ስሜት እንደተጫነው አሳዛኝ ክስተት የሚያየው ከሆነና ሌላው ደግሞ ከዕድገት ፈላጊነትና ከዓለማቀፋዊነት ንቃተ ሕሊና ጋር የሚያያይዘው ከሆነ አገሪቱ እምቅ ችሎታ ያለው ወሳኝ የሰው ኃይል የምታጣበትን ይህን ሂደት በትምህርትና በተቋማዊ ሥርዓት እንዴት እንፍታ?" የሚለው ጥያቄ ላይ የሚያግባባ መልስ ላይ ልንደርስ አንችልም። ምክንያቱም እንኳን መፍትሔው ላይ በችግሩ ችግርነት ላይም አልተግባባንምና። ሌላ ምሳሌ ልጨምር። አንዱ አገራችን ጥሬ የተፈጥሮ ሀብቶችን ወደ ውጭ አገር በብዛት በመላክ የውጭ ምንዛሪ የምታስገኝበትን ሂደት ለዕድገት ወሳኝ እንደ ሆነ የምጣኔ ሀብት መመሪያ የሚያየው ከሆነና ሌላው ደግሞ በዚህ ሂደት አብዛኛው ደኃ በራሱ አገር ገበያ ከውጭ ምንዛሪ ባልተናነሰ ተመን የሚያስፈልገውን ጥሬ ዕቃ ለመግዛት መገደዱን እንደ ምጣኔ ሀብት ቀውስ የሚያየው ከሆነ ሁለቱን የሚያስታርቅ ምን ዓይነት የሚያግባባ የምጣኔ ሀብት ሥርዓተ-ትምህርት ሊኖረን ይችላል? እንዲህ ባለ ሂደት በፍላጎቶች ግጭት (conflict of Interest) ተጠላልፈን ስለምንገኝ ችግር ፈቺ ትምህርትንና ተቋማዊ ሥርዓትን በሚመሳስሉ ታላላቅ እሳቤዎች ላይ የጋራ መግባባት ለመድረስ እጅግ እንደ ከበደን እንገኛለን። ስለዚህ በቅድሚያ "ችግር ያለበት ማኅበረሰብ" የምንለው ምን ዓይነት እንደሆነና "ችግር የሌለበት የምንፈልገው ጥሩ ማኅበረሰብ የምንለው ደግሞ ምን ዓይነት ሁለንተናዊ አቋም ላይ ያለ ማኅበረሰብ እንደ ሆነ በግልጽ መለየት መቻል አለብን። በዚያ ላይ ስምምነት ላይ መድረስ ከተቻለ ችግሩን የመፍታት ተነሳሽነት ለብዙ ግራ መጋባት በቀላሉ ይመጣል።

በውጭ ተሞክሮዬ ውጤታማ የሆኑ የትምህርት ተቋማት ለውጤታማነታቸው ምክንያት የሆኑ የአስተሳሰብ መንገዶቻቸውን አስመልክቶ ያስተዋልኳቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ለምሳሌ፡- በትምህርቱና በማኅበራዊ ሳይንሱ ዘርፍ ባሉ መርኃ-ግብሮች ሁሉ። በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተደጋግሞ የሚነሳው አንዱ ዋና ጽንሰ-ሃሳብ ለሁሉ የሚበጅ የጋራ ጥቅምን ("the common good") ማስጠበቅ የሚባለው መርህ ነው። የመንግሥትና የሕዝብ ተቋማት ከግል ተቋማት ጋር ተፎካካሪ ሆነው ለብዙው ሕዝብ ተደራሽ የሆነ አገልግሎት ሊያበረክቱ የሚችሉባቸውን መንገዶች ማጠናከርና የግል ተቋማት ኃይል ያለመጠን አድጎ የምጣኔ ሀብት፣ የመረጃ ፍትሃዊነትና የማኅበራዊ ደረጃ ልዩነት እንዳይሰፋ ለማድረግ እልህ አስጨራሽ የሆነ ትግል ማድረግ እንደሚገባ እየተጠቃቀሱ በየኮርሱ የሚያደርጉበት የሃሳብ ፍጭት ሁልጊዜ ይገርመኝ ነበር። አያቷ ያስተዳድሩት የነበሩትን የሕዝብ/የመንግሥት ትምህርት ቤት አባቷ ተረክበውት በርእሰ መምህርነት ሲያገለግሉበት ከቆዩ በኋላ እርሷ በፈንታዋ ተረክባ ለረዥም ዓመታት በርእሰ መምህርነት በመሥራት ተፎካካሪ ሆኖ እንዲቀጥል ካደረገች ርእሰ መምህር ጋር ለማውራት በአንድ ወቅት ዕድሉ ገጥሞኝ ነበር። ሴትዮዋ ከአያቷ የወረሰችውን መኖሪያ ቤት ሳይቀር በቅርስነት የምታይና በየጊዜው ከማስጠገንና ከማስፋት በስተቀር ለማፍረስም ሆነ በሌላ ቤት ለመኖር ፍላጎት ጨርሶ ኖሯት የማታውቅ የምትገርም ርእሰ-መምህር ናት። የአስተሳሰብ መንገዷን ለመረዳት ስሞክር ያገኘሁት ግንዛቤ ይህ ውሳኔዋ "አገር ማለት ሀብታምን ከድኃ ሳይለዩ ኹሉን በእኩልነት አገልግሎት የሚሰጡና ትውልድን አልፈው የሚሻገሩ የሕዝብ ተቋማት ናቸው" የሚል ከብረት የጠነከረ ጠንካራ አመለካከት ያላት መሆኗን ለመረዳት ችያለሁ። ይህ የርሷ ብቻ ሳይሆን የብዙ መምህራንና ፕሮፌሰሮች (በተለይ "democrat ነን" የሚሉት) አስተሳሰብ እንደሆነ እያደር ለመረዳት በቅቻለሁ። በእኛ አገር ግን ምዕራባውያን የምንላቸው ንጹህ ካፒታሊዝምን ብቻ የሚከተሉ ሕዝቦች እንደሆኑ አድርገን ነው። "ዘመናዊ አስተሳሰብ" ማለትም በዚህ ረገድ privatization ብቻ ሊመስለን ይችላል። እውነታው ግን ያ አይደለም። ታድያ በዚህ መነጽር ስንመለከተው በእኛ አገር ተማሪዎች ከተመረቁ በኋላ በግል ሳይሆን በሕዝብ /በመንግሥት ተቋማት ውስጥ ገብተው ጥራት ያለው ሥራ በመሥራት የአገሪቱን ሚዛናዊና የተረጋጋ ህልውና ማስጠበቅን እንደ አንደኛ ምርጫቸው እንዲያዩት ለማሳመን የሚያስችል የውይይት አጀንዳ በክፍል ውስጥ ብንፈጥር ብዙ ተማሪዎችን የሚኮረኩሩና ነባራዊ ኹኔታውን አጥብቀው ለመመርመር የሚያስችሉ ዕድሎችን እንደምናስገኝላቸው እርግጠኛ ነኝ። ሆኖም እንዲህ ላሉ ጠንካራ የአቅጣጫ ለውጥ ለማድረግ የሚጋብዙ ወሳኝ አጀንዳዎች ጊዜያችንን ስናውል እምብዛም አንታይም። ባሁን ጊዜ cost sharing እና በተለያየ ዘርፍ የሚመረቁ ተማሪዎችን በመንግሥት ተቋማት ቢያንስ ለተወሰኑ ዓመታት እንዲያገለግሉ ለማድረግ የሚወጡ የጊዜ-ገደብን የተመለከቱ ደንቦችን በምሳሌነት ብንመለከት ጉዳዩን ዘላቂ የሆነ የcommon good ጥያቄ ሳይሆን፡ ጊዜያዊ የሆነ fair share ማስጠበቂያ የአስተዳደርና የደንብ ጉዳይ ብቻ አድርገን እየተመለከትነው እንደሆነ ያሳየናል። በዚህ ዓይነት አስተሳሰብ ውስጥ ሆነን ተማሪን አሳታፊ የኾኑ የውይይት መድረኮችን መፍጠር አንችልም። ምክንያቱም "ተማሪን ማሳተፍ" ማለት "ተማሪን ማስለፍለፍ" ማለት ሳይኾን የራሱንና የአገሩን ህልውና አስመልክቶ ያሉ ወሳኝ አጀንዳዎችን ግልጽልጽ አድርጎ ከፊቱ በማስቀመጥ አጥብቆ እንዲያስብ ማድረግ ማለት ነውና። ስለዚህ ችግር-ፈቺ ዜጋ የሆነ ትውልድ ለማፍራት ችግሮች ላይ አጥብቆ በማሰብ መፍትሔ ለመጠቆም ጠንካራ አቋም ያዳበሩ ብዙ መምህራን ያስፈልጉናል።

**ናይል፡-** **የአካዳሚክ ሠራተኛ ማለት በአንድ ተቋም 75 ፐርሰንት የሥራ ጊዜው የማስተማር ቀሪ 25 ፐርሰንት የሥራ ጊዜው የምርምር ሥራ የሚሠራ ነው ይባላል። ነገር ግን በሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ሲታይ ምሁራን በተለያዩ ኃላፊነትና ግላዊ ስራ ተጠምደው ጊዜአቸውን ያሳልፋሉ ይባላል። ስመሆኑ የዚህ ችግር ምን ሲሆን ይችላል ብለው ይገምታሉ? በሠለጠነው አለም ያለው ነባራዊ ሁኔታስ ምን ይመስላል?**

*ዶ/ር መስከረም፡-* ምሑራን በተለያዩ ምክንያቶች ከምርምር ሥራዎች ሊርቁ ይችላሉ፤እንደተባለው በግል ሥራና በኃላፊነት በመጠመድም ጭምር። ከዚህ በተጨማሪ ግን በአገራችን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ምርምርን እንደ አንድ ሊሟላ እንደሚገባው አካዳሚያዊ ግዳጅ እንጂ እንደ ግል ጥያቄዎቻቸውን መመለሻ መንገድ አለማየታቸው "በጥናትና ምርምር ረገድ ሊያበረክቱ የሚችሉትን አስተዋጽኦ ገድቦባቸዋል "የሚል የግል አመለካከት አለኝ። ይህም ማለት ነው ብትዩኝ ለምሳሌ፡- በኃላፊነት የምንሠራው ሥራ ወይም የግል ጉዳያችን ራሱ ከሙያችን ጋር የሚገናኝና በሙያችን መነጽርነት ሊጠና የሚገባው የሕይወታችን ክፍል እንደ ሆነ አድርገን ብዙ ጊዜ አገናኝተን የምናስብ አይመስለኝም። ለብዙ ምሑራን ማኅበራዊ ሕይወት ሌላ ነው፤ የቢሮ ኃላፊነት ሌላ ነው፤ ማስተማር ሌላ ነው፤ ጥልቅ የሆኑ የግል ጥያቄዎቻቸው ደግሞ ሌሎች ነገሮች ናቸው። እዚህ ላይ ደግሞ ምርምርን ብንጨምርበት ብዙ ምሑራን ስለ አምስተኛ የሕይወት ዘርፍ እያወራን እንደሆነ እንደሚያስቡ እገምታለሁ። ነገር ግን እውነታው ነገሮች ብዙ ጊዜ እርስ በርሳቸው የተያያዙ ናቸውና ሁለንተናዊ የሆነ የአስተሳሰብ ልምድ ("holistic thinking") ያስፈልገናል። ምሑራን ለራሳቸው ከሚገርማቸውና "አንገብጋቢ ነው" ብለው ከሚያስቡት ግላዊና ቤተሰባዊ የሕይወት ጥያቄ በመነሳት ብዙ ምርምሮችን ሊሠሩ ይችላሉ። የምርምሩ ውጤት ተጠቃሚ ራሳቸውን ከማድረግ መጀመር አለባቸው። በዚህ አካሄድ ለመጠየቅ "safe" ያልሆኑ ብለው የሚያስቧቸውን ጥያቄዎች ጭምር በምርምር ጥያቄነት በማንሳት ከሚያዘርፋቸው ጋር አያይዘው ሊያጠኑት ይገባል። እንዲህ ሲሆን ምርምር ባህል ይሆናል።

ለሦስተኛ ዲግሪ ማሟያ የሠራሁትን የራሴን ጥናት በምሳሌነት ባነሳ ጥናቱ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴ ጀምሮ አብሮኝ ለረጅም ዓመታት የኖረ የራሴን ጥልቅ ጥያቄ ለመመለስ ያደረግሁት ጥናት ነበረ እንጂ ለዲግሪ ማሟያነት ብቻ በእኔ ዘርፍ ያሉ ምዕራባውያን ምሑራን የሚያነሷቸውን ጥያቄዎች እኔም በማንሳትና በመረጃ አስደግፌ መልስ በማስቀመጥ እኔም የምርምር ሥራን አካሄድ እንደማውቅበት ለማሳየት ያደረግሁት ጥናት አልነበረም። እንደዚያ ቢሆን ኖሮ ሦስተኛ ዲግሪዬን ለመጨረስ የሚያስፈልገኝ ጊዜ አምስት ዓመት ተኩል ሳይሆን ሦስት ዓመታት ብቻ ይሆን ነበር። ከዚህ የተነሳ "ለምንበራስ ሽላይ ሥራ ትጨምሪያለሽ? አማካሪ ፕሮፌሰር ባስጀመረሽ ፕሮጀክት ላይ ቀጥለሽ ሠርተሽ በጊዜ አትመረቂም?" ብለው ሊጠይቁኝ የተገደዱ መምህሮቼም ነበሩ። በሃሳቡ ሳልስማማ ቀርቼ ኋላ ላይ የመረጥኳት ሌላኛዋ አማካሪዬም፡ "wow! You chose such a hard task for yourself" ነበር ያለችኝ። "ያንቺን የምርምር ውጤት እየጠበቀ ያለ የምሁራን ቡድን ኢትዮጵያ ተቀጥረሽ የነበረበት ዩኒቨርሲቲ ውስጥ አለ ወይ?" ብላ ጠይቃኝም ታውቃለች። መልሴ "አዎ" ነበር። "ማን" ብላ በጠየቀችኝ ጊዜ መልሴ "እኔ ራሴ" የሚል ነበር። ምክንያቱም ወደ አሜሪካ የሄድኩት ስለ ስኮላር ሺፕ ሳመለክት ያነሳሁትን የራሴን ጥያቄ ለመመለስ እንጂ የትኛው ፖሊሲ አውጪ በምን መልኩ እንደሚተረጉመው ግልጽ በማይኾንበት መልኩ ሪፖርት የማቀርብበትን የኔ ያልሆነን "የወቅቱን" የአሜሪካውያን ምሑራንን ጥያቄ ኢትዮጵያውያን የምርምር ተሳታፊዎችን መልምዬ በመጠቀም ለመመለስ አልነበረምና። በዚህ አቋሜ በመጽናቴ ምክንያት በመጀመሪያ ችግር የገጠመኝ ቢሆንም በስተመጨረሻ በኮሌጁ መምህራን ከፍተኛ ግምት የተሰጠው ጠንካራ የሆነ ምርምር ልሠራ በቅቻለሁ። ወደ መጽሐፍነት ተለውጦ ለሰፊ ንባብ መብቃት እንዳለበት የጠቆሙኝ ነበሩ። "ብዙ ትምህርት አግኝቼበታለሁ" ያሉኝም አሉ።

ወደ ገጽ 13 ዞሯል

# የጉዞ ማስታወሻ

ከባለፈው ወር እትም የቀጠለ

በአምሳሉ ጥላሁን

ከምሽቱ 12:30 ላይ ወልድያ ደረስን፡፡ ተማሪዎችም ወልድያ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ገብተው ማደር ስላለባቸው መኪናው ዋናውን መንገድ ለቆ በስተቀኝ በኩል ወደሚገኘው ወደ ወልድያ ዩኒቨርሲቲ በር ታጠፈ፡፡ በሩ ላይ እንደደረስን የዩኒቨርሲቲው የጥበቃ ሰራተኞች አክብሮት በተሞላበት ሁኔታ ‹‹ምን እንርዳችሁ›› በማለት ተቀበሉን፡፡ አቀባበላቸው ደስ ይላል፡፡ ስርዓታቸውና ትህትናቸው ለሌሎች የዩኒቨርሲቲዎች የጥበቃ ሰራተኞች ምሳሌ የሚሆኑ ናቸው፡፡ መሽቶ ስለነበር ወደ ጉዳያችን ገባን፡፡ ለዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች አገልግሎት ኃላፊ ስልክ ደወለን ስልኩ ግን አይሠራም፡፡ ምን ይሻላል ተማሪዎች የግድ ማደሪያ ማግኘት አለባቸው፡፡ ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት መደወል ግድ ሆነ፡፡ ስልክ ደወልኩ ‹‹ሀሎ ሀሎ›› አሉኝ ፕሬዚዳንቱ ነበሩ ‹‹ጤና ይስጥልኝ ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ነው የምደውለው›› አልኳቸው፡፡ ‹‹እሽ ምን ልርዳህ›› አሉኝ፡፡ ይቅርታ ፕሮፌሰር ተማሪዎችን ይዘን ወደ ዩኒቨርሲቲያችሁ መጥተናል እና ለእነሱ የሚሆን ማደሪያ እንዲፈቀድልን እባክዎትን ፍቃድ ይስጡን ብዬ ነው፡፡ እሽ ችግር የለም አንድ አምስት ደቂቃ ጠብቁኝ የሚመለከታቸውን እልካለሁ አሉኝ፡፡ አምስት ደቂቃ ሳይሞላ የሚመለከተው አካል ተላከልን፡፡ እንዲህ ነው ቀልጣፋ የማህበረሰብ ቁርጠኛ አገልግሎት አልኩኝ፡፡

ተማሪዎችን አስገብተን የእኛን መኝታ ቤት ፍለጋ በባጃጅ ለመሄድ ተገደድን፡፡ መኪናችሁስ? እንዳትሉኝ ብቻ፡፡ ለተማሪዎች የተዛዘ ስለነበር ከዚያው ትተን መጣን፡፡ ልክ አንድ ሁለት እርምጃ እንደተራመድን አንድ ቲዎታ መኪና መንገድ ዳር ቆማለች፡፡ የሥራ ባልደረባዬ አቶ ታምራት ወደ መኪናዋ ጠጋ ብሎ ‹‹ወደ ከተማ ብትወስዱን?›› አላቸው፡፡ ከሾፌሩ አጠገብ የተቀመጠ አጠር ወፈር ብሎ ቦርጩ ገፋ ያለ እድሜው 45 ዓመት አካባቢ የሚገመት ሰውዬ መኪናው የመንግስት ስለነበር ‹‹ይህ መኪና እኮ የሁላችንም ነው ኑ ግቡ›› አለን፡፡ ‹‹እናመሰግናለን›› ብለን በደስታ ወደ ውስጥ ገባን፡፡ ሾፌሩ ወደ መሃል ከተማው እየገሰገሰ ነው፡፡ በአምሮዬ እዚች ሃገራችን ውስጥ የመንግስት ገንዘብ የግል የሚመስላቸው ባለስልጣኖችን አሰብኩና ከዚህ ሰውዬ ጋር አነፃፀርኳቸው፤ ምንም የማያውቁንን ሰዎች የመንግስት ገንዘብ የህዝብ ነው ብለው በማሰብ እንድንገለገል መፍቀዳቸው፤ በጣም ይገርማል፡፡ ከገብስ መሐል እንክረዳድ አይጠፋም እንደሚባለው አይነት ናቸው ማለት ነው፤ በዚህ ሃሳብ ውስጥ እንዳለሁ ጋቢና ላይ ያለው ሰውዬ ‹‹እንግዳ ትመስላላችሁ ከየት መጣታችሁ ነው?›› አለኝ፡፡ ‹‹አዎ እንግዳ ነን፡፡ ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ›› አሉኳቸው፡፡ ‹‹ባሕር ዳር ከተማ በጣም ነው የምትመቸኝ፡፡ በክልል አመራርነት አገልግያለሁ፡፡ ከተማዋ አሁን በጣም ተለውጣለች›› አሉኝ፡፡ ‹‹አዎ በጣም እንጂ›› አልኳቸው በልበ ሙሉነት፡፡ ለምን እያዳላህ ነው እንዳትሉኝ በክልላችን ካሉት ከተሞች ውስጥ ማንም እንደማይወዳደራት በማሰብ ነው፡፡ ‹‹አዎ እውነት ነው›› አሉኝ፡፡ ሆቴሎች ወደሚገኙበት አካባቢ ስለደረስን አመስግነን ከመኪናቸው ወረድን፡፡ በአካባቢው ብዙ አልጋ ቤቶች ስላሉ ሳንቸገር ሆቴል በቀላሉ አገኘን፡፡ እራታችን ከዚያው ሆቴል ውስጥ ተመግበን ወደ መኝታ ክፍላችን ገባን፡፡ ያደርንበት አልጋ በጣም ፀጥታ የሰፈነበት ስለነበር ከእንቅልፌ የነቃሁት በጓደኞቸ ቅስቀሳ ነበር፡፡ ምን አለበት ዛሬን የእረፍት ቀን ቢያደርጉት እያልኩ ወደ እጅ መታጠቢያ ክፍል በመሄድ እጄንና ፊቴን ስታጠብ እንቅልፌ ለቀቀኝ፡፡ ሾፌራችን በሩ ላይ ተማሪዎችን ይዞ በክላክስ ጠራን፡፡ ልብሶቸን ይዤ ወጣሁ፤ ደግሞ ዛሬ የት ይሆን የምንሄደው? አልኩት ሾፌሩን፡፡ ‹‹ምነው እስካሁን? እንዴ የጥዋት ጉዞችን አስረፈድክብን እኮ›› አለኝ፡፡ በጣም ይቅርታ ደክሞኝ ስለነበር መሰለኝ፡፡ ‹‹አይዞህ በርታ በል እንጂ›› አለኝ ሳቅ እያለ፡፡ ጉዞ ተጀመረ ወልድያ ከተማ ወደ አስር ኪ.ሜትር ርቀት ከሄድን በኋላ ከመኪና እንድንወርድ ከመንገዳችን በስተቀኝ በኩል የተዘራውን ማሽላ ሰብል ተማሪዎች እንዲያዩትና ጥያቄ ወይም ማብራሪያ የሚያስፈልገው ነገር ካለ እንዲጠይቁ ዶ/ር አብርሃም ጋበዟቸው፡፡ ተማሪዎችም ወደ ማሽላው ማሳ አቀኑ፡፡ ማሽላው ፍሬ ሳያፈራ ገና በቅጠሉ እንደደረቀ አየን፡፡ ተማሪዎች እርስ በራሳቸው ‹‹በጣም የሚያሳዝን ነው ምንም አይነት ፍሬ አልያዘም!›› እያሉ ተገረሙ፡፡ መምህር አብርሃም ግን ከዚህ በፊት መጥተው አካባቢውን ስላዩት ‹‹ገና ምኑን አያችሁትና›› አሉ በሎሆሳስ ድምፅ፡፡ ተማሪዎችም ምንም አይነት አስተያየት ሳይሰጡ ወደ መኪናው አመሩ፡፡

ሁሉም ከገቡ በኋላ ዶ/ር አብርሐም መብራት ተማሪዎችን ‹‹ከዚህ በኋላ መኪናው ቀስ ብሎ ስለሚሄድ አካባቢውን በደንብ እያያችሁ ሂዱ›› አሉ፡፡ በመኪናው መስኮት በኩል ወደ ውጭ ማየት ጀመርኩ፡፡ አልፌው አልፌው ለምልመው የሚታዩት የጃትሮፋ እንዲሁም የግራር ዛፎች እየተመለከትሁ ጉዞችን ቀጠለ፡፡ ከዚህ በፊት በተለየዩ ሰብሎች ተሸፍኖ የሚታይ የነበረው የራያ ቆቦ መሬት እርቃኑን ይታየኝ ጀመር፡፡ ራያ መሬት የማኛ፣ ጤፍና ሰርገኛ ጤፍ በሄክታር ከ20 እስከ 30 ኩንታል፣ ማሽላ፣ ገብስ፣ በቆሎ እና ሽንኩርት በሄክታር ከ30 እስከ 60 ኩንታል እንደየ ሰብሉ አይነት ያገኙ እንደነበር የገለጸችልኝ የራያ ቆቦ ተወላጅ የሆነችውና የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የአደጋ መከላከልና የምግብ ዋስትና ጥናት ተቋም የ3ኛ ዓመት ተማሪ የሆነችው መሰሉ አርብሲ ናት፡፡ ድርቁ የተከሰተው የራያ ቆቦ ገበሬ በበልግ ወራት ይዘንብ የነበረው ዝናብ ሳይዘንብ ሲቀር ሁሉም የክርምቱን ዝናብ በጉጉት መጠበቅ ጀመረ፡፡ ጊዜውም ከወር ወር እየተሻገረ የሐምሌ ወር ገባ፡፡ የሐምሌ ወር በአብዛኛው በኢትዮጵያ አካባቢዎች ዝናብ በጣም የሚዘንብበት ወቅት ነው፡፡ በራያ ቆቦ መሬት ላይ ፊቱን አዞረበት፡፡ የራያ አርሶ አደር ለሊትም ሆነ ቀን ወደ ሰማይ መመልከት ብቻ ሥራቸው ሆነ፡፡ ምን ይደረግ እንግዲህ እንደሰው አይከሰስ፣ አይወቀስ፡፡ እርሱ እንደ ቸርነቱ ፊቱን እንዲመልስ ከመለመን ውጭ፡፡ የነሐሴ ወርም እንደ ሰኔ እና ሐምሌ ወር ፀሐይ ብቻዋን በነፃነት አምርራ ጨረሯን እየለቀቀች ጭካኔዋን አሳረፈችባቸው ምንም የዝናብ ጠብታ ሳይታይ ወቅቱ አለፈ፡፡ አርሶ አደሩም ተስፋ ቆረጠ፡፡

በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንደሚባለው ሁሉ ድርቁ በተከሰተባቸው አካባቢዎች በሙሉ የውሃ ምንጮች ከጊዜ ወደ ጊዜ ደረቁ፡፡ በየመንገዱ አርሶ አደሩ በግመሉ እና በአህያው ጀሪካን ጭኖ ውሃ ፍለጋ ይማስናል፡፡ ተሳፋሪው ፀጥታና ሀዘን በተቀላቀለበት የፊት ገፅታ ተዋጠ፤ መኪናችን ውስጥ ትካዜ ሰፈነ፡፡ በዚህ ስሜት ውስጥ እንዳለን ቆቦ ከተማ ገባን፡፡ ወደ አዲስ ከተማ በገባን ቁጥር በጭብጨባና በፉጨት ከመኪና ይወርዱ የነበሩት ተማሪዎች እዚህ ከተማ ስንገባ ግን በዝምታ እንደተዋጡ ነበር፡፡ ወደ ገጠር ለምናደርገው ጉብኝት የሚያግዘን አቶ ተመስገን የተባለ ባለሙያ ተቀላቅሎን ወደ መቀሌ መውጫ

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

## Save the Oxen ...

continued from page 6

the agriculture sector will be exacerbated by the shortage of oxen unless urgent solution is given. In addition, we will be challenged if we cannot replace the use of oxen with machines affordable to the poor.

Leaving the task of investigating the problem in depth for researchers in the field, let me now, pinpoint my practical observations to figure out the magnitude of the real potency of the danger in the future. First, the present trends show that oxen are not selected purposefully. To illustrate, I think, best ploughing oxen available in the market should not be slaughtered although the farmer has the right to sell. In connection, the price of oxen has been increasing alarmingly from time to time, which indicates that it may not be affordable for the poor. Consequently, many farmers may be displaced from their farm for survival.

On the whole, the backbone of our economy will be at risk, for the reasons I discussed above. Therefore, I argue that we have no more choice except organizing a multilateral "Save the Oxen" promotion, and striving tirelessly for its achievement.




Fig 1: Save the Oxen!



Fig 2: Turn the Oxen back to their Original Job!

# “ነፃ አውጪው” ማን ነው? …

ከገጽ 7 የዞረ

እንዴለለው አጫወተኝ፡፡ “ለምን?” አልኩት፡፡ “በግራም ስለሚሸጥ፣ ድሀውም-ሀብታሙም እኩል የሚቅመው ጫት ቢኖር እሱ ነው፡፡ ልዩነቱ ሀብታሙ እስከ መቶና ከዚያ በላይ ግራም ሲቅም ድሀው ቢያንስ ሀያ አምስት ግራም ይቅማል፡፡ ‘አስር ግራም’ ስጡኝ ብትል አንተን አይነስህ እንጂ ሻጮቹ ጉዳያቸው አይደለም፤ መዝነው ይሰጡሀል፡፡ እዚህ ግን ከተወሰነ መጠንና ዋጋ በታች ንቅንቅ የለም፡፡”…

ቀደም ሲል እንደ ተገለፀው የባህር ዳር ጫት አዲስ አበባ፣ ደሴ፣ ወልድያ፣ ወዘተ ከገባ ቆይቷል፡፡ የሚሸጠው ደግሞ - የትም ቦታ ቢሆን - እንደ ወጥ ቅመም በግራም እየተመዘነ ነው፡፡ ይህ የአሻሻጥ መንገድ “የተሳታፊውን” አይነትና ስብጥር ለማሳደግ ረድቶታል፡፡ ስርጭቱንና “የተሳታፊውን” አይነት ለማሳደግ የረዳው ሁለተኛው ምክንያት የዋጋው መጠን ነው፤ እንደ ሰማሁት በአብዛኛው ቦታ ዋጋው ተመሳሳይ ነው፡፡ ሶስተኛው ምክንያት ባህር ዳር ከአቅሚ በላይ (ማለትም ቃሚዎቿ ሊቅሙ ከሚችሉት በላይ) ለማምረት መቻሏ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ማለትም ከፍተኛ የጫት ምርት እንዲኖር ያስቻለው፣ ከሌላው አካባቢ በተለየ ሁኔታ፣ የባህር ዳርና አካባቢው ጫት ቀንበጡ ብቻ የሚለቀም/የሚቆረጥ መሆኑ የአንበሳውን ድርሻ ይይዛል፡፡ በሌላው አካባቢ (ወሎ፣ ሀረር፣ ደቡብ፣ ወዘተ) የሚመረተው ጫት ከነዛላው ነው የሚቆረጠው፡፡ ስለሆነም ቀንበጡ ብቻ ሳይሆን ዛላው (ቅርንጫፉ) ጭምር እስከሚያድግ መጠበቅ ግድ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ያለ ጥርጥር ጊዜ ይወስዳል፡፡ የባህር ዳርና አካበቢው ጫት ግን ቀንበጡ ብቻ የሚለቀም ስለሆነ በሶስት ሳምንት አንድ ጊዜ ይደርሳል፤ ሁኔታው ከተመቸው በሁለት ሳምንት ውስጥም ለለቀማ ሊደርስ ይችላል፡፡

ብዙዎቹ ከባህር ዳር ውጭ ያሉ የሩቅ “አገር” ደንበኞች ማለትም በአዲሳባ፣ በደሴ፣ በጎንደር፣ በወልዲያ፣ በመቐሌ ከተሞች የሚገኙ የባህር ዳር ጫት ቃሚዎች፣ ቀደም ሲል በየአካባቢያቸው ይሸጥ የነበረው ጫት፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ ዋጋው እየናረ ሲመጣ፣ በተለይም ደግሞ በበጋ ወቅት ዋጋው የንረቱን ጣሪያ ነክቶ እንደ ትኩስ ገንፎ አልቀመስ ሲል፣ በአንፃራዊነት በርካሽ ዋጋና በፈለጉት መጠን ወደሚሸጠው የባህር ዳር ጫት ፊታቸውን ሙሉ በሙሉ ያዞሩ ናቸው ማለት ይቻላል፤ ወይም በዘመኑ አነጋገር “ብሎ መውሰድ” ይቻላል፡፡ እንደ ደሴዎቹ ቃሚዎችና አዲስ አበባ እንደ ገባው የቀድሞ የስራ ባልደረባዬ፣ የጋሌሳ፣ የበለጬና መሰል ጫቶች ዋጋ ያንገፈገፋቸው ቃሚዎች፣ እስከ ደጃቸው ድረስ የሄደውንና በተመጣጣኝ ዋጋ፣ ለሁሉም እንዳቅሙ የሚቀርበውን የባህር ዳርን ጫት ከጥሩ አማራጭ ቆጥረው ቢቅሙ፣ የደንበኝነት መዝገባቸውን ወደ ባህር ዳር ጫት ቢያዛውሩ ምኑ ይደንቃል? የሚደንቀው ነገር፣ የባህር ዳርን ጫት፣ “ነፃ አውጪ” በማለት የማሞገሳቸው፣ የማንቆላጰሳቸው ጉዳይ ነው፡፡

ይህን መጣጥፍ እያገባደድኩ እያለሁ ለባህር ዳር ጫት “ነፃ አውጪ” የሚለው ሽልማት ከየት እንደ መጣ፣ በዚያ የመቐለ ጉዟችን የባህር ዳር ጫት “ነፃ አውጪ” መባሉን የነገረንን ባልደረባችንን ጠየኩት፡፡ “ነፃ አውጪ” በማለት ያንቆላጰሱት ከባህር ዳር ውጭ ያሉ ቃሚዎች መሆናቸውን አረጋገጠልኝ፡፡

እርግጥ ነው፣ ብዙዎቹ ከባህር ዳር ውጭ ባሉ ከተሞች የሚገኙ የባህር ዳር ጫት ቃሚዎች፣ በአካባቢያቸው በሚገኝ ጫት ላይ ያመፁ ቃሚዎች ናቸው፡፡ በአካባቢያቸው ወይም ከአካባቢያቸው በቅርብ ርቀት የሚመረት ጫት ከሚያሳድርባቸው የዋጋ ጭቆና “እምቢ፣ አልቅምህም!” በማለት ራሳቸውን “ነፃ ያወጡ ጀግኖች”፡፡ አሳዛኙ ነገር፣ ይህ ጀግንነታቸው ወንዝ የማያሻግር ከመሆኑ ላይ ነው፡፡ “ለምን?” ቢሉ እራሳቸውን ነፃ ያወጡት፣ ዋጋ በማስቀነስና የጫት አይነት በመቀየር ብቻ ነውና፡፡ ከጫት ቅኝ ግዛት ራሳቸውን ነፃ ለማውጣት ግን አልተቻላቸውም፡፡ ካሉበት የሱስ ቅኝ ተገዢነት አንፃር ሲታይ፣ ጀግንነት እሱ ነበር፡፡ አዎ - በአንፃራዊነት ከዋጋ ጭቆና ነፃ ወጥተዋል፤ ከሱስ ጭቆና ግን ነፃ አልወጡም፡፡ እንዲያውም የየአካባቢያቸው ጫት ዋጋውን በመስቀል፣ ሳይወዱ በግድ ከሱስ ነፃ ቢያወጣቸውም፣ ወድደውና ፈቅደው የባሕር ዳር ጫት የጭቆና ባሪያ፣ የባህር ዳር ጫት ቅኝ-ተገዢ ሆነዋል፡፡

ከዚህ የከፋው አሳኝ ነገር፤ ከሱስ ባርነት እንዳይላቀቁ፣ በሱስ ቅኝ ግዛት ስር እንዲማቅቁና እድሜያቸውን እንዲገፉ ያደረጋቸውን የባሕር ዳርን ጫት “ነፃ አውጪ” ማለታቸው ነው፡፡ ታላቁ ምፀትም ያለው እዚህ ጋር ነው - አንድ ህብረተሰብ በጉልበቱ ስር አድርጉ፣ በቁጥጥሩ ስር አስገብቶ በሱስ ቅኝ ግዛቱ ስር ያዋለውን እፅ “ነፃ አውጪ” ብሎ ሲያንቆላጵስ፡፡ ይህ አገላለፅ ፖሎ ፍሬይሬ (Paolo Freire) “መጨቆናቸውን ያላወቁ ጭቁኖች” በማለት “ከተረባቸው” የህብረተሰብ ክፍሎች የከፋ አይደለምን? የፍሬይሬ “ሰዎች” ችግር መጨቆናቸውን አለማወቃቸው ነው፤ ከዚህ አልፈው ግን “ነፃ የወጣን ህዝቦች ነን” የሚል ምስክርነት አልሰጡም፡፡ የእኛዎቹ “ሰዎች” (ቃሚዎች) ግን፣ በሱስ ቅኝ ግዛት ስር መውደቃቸውን “ካለማወቅ” አልፈው፣ ቀጥቅጦ እየገዛቸው ያለውን አደገኛ እፅ “ነፃ” አውጪ በማለት እስከማንቆላጰስ ደርሰዋል፡፡

## ምን ይደረግ?

ከዚህ ሁሉ የከፋውን ጉዳይ እናንሳ፤ በባህር ዳርና በአካባቢው ባሉ የገጠር ቦታዎች ጫት የሚመረትበት ቦታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ በመሄድ ላይ ነው፡፡ የሰብልና የሌሎች አትክልት ቦታዎች በጫት ተክል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተተኩ ነው፡፡ ለምሳሌ የዛሬ ዘጠኝና አስር አመት አካባቢ ከጣና ዳርቻ፣ ዘጌ አካባቢ በሚያስጎመዡ የማንጎ፣ የፓፓያና የአቦካዶ ተክሎች ተይዘው የነበሩ እርሻዎች ሙሉ ለሙሉ በሚያስብል ሁኔታ በጫት ተክል ተተክተዋል፡፡ አንድ በጫት ንግድ ላይ የተሰማራ ወጣት እንደ ነገረኝ፡፡ በባሕር ዳር ዙሪያ ባሉ የገጠር መሬቶች፣ “ለውሀ ቅርበት ያለው ቦታ ሁሉ የጫት ተክል እየተተከለበት ነው ያለው፡፡” ወጣቱ እንዳጫወተኝ እንዳውም አሁን-አሁን ከምንጭ ወይም ከወንዝ በ1200 ሜትር (1.2 ኪሎ ሜትር) ርቀት ላይ ጭምር ጫትን ማልማት ተጀምሯል - የፕላስቲክ ቱቦ (ፒቢሲ) በመሬት ውስጥ በመቅበር ውሀውን በሞተር ሀይል እየገፉ በመውሰድ፡፡ በሌላ አገላለፅ የጫት ተክል የውሀ ፍጆታንም በመሻማት ላይ ነው - ሌሎች የአትክልት፣ ፍራፍሬና የእህልን አይነቶችን ለማምረት ሊውል የሚገባውን ውሀ በመንጠቅ፡፡

የባሕር ዳር ጫት በባሕር ዳርና አካባቢው የምርት አድማሱን በማስፋት ላይ እንዳለ ሁሉ፣ የሽያጭ አድማሱንም ቀስ-በቀስ በማስፋፋት ላይ ነው - ነገ-ከነገ ወዲያ ብዙዎቹን የሀገሪቱን ከተሞች እንደማያዳርስ ማረጋገጫ የለንም፤ ብዙዎቹን የሀገሪቱን ቃሚዎች “ነፃ እንደማያወጣ” ሳይሆን ከቅኝ ግዛቱ ስር እንደማያውል እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡ የመንገድ ግንባታ መስፋፋትና የመኪና ትራንስፖርት መቀላጠፍ ሰሜን፣ ሰሜን ምእራብና ሰሜን ምስራቅ ኢትዮጵያን ለማዳረስ ጥሩ አጋጣሚ እንደ ፈጠረለት ሁሉ፣ የባቡር ትራንስፖርት መዘርጋት እንደ ቅንጪ አረም በመላ ሀገሪቱ ለመስፋፋት መልካም አጋጣሚ የሚፈጥርለት ለመሆኑ ብዙም አያጠራጥርም፡፡

ከዚህ አንፃር ዘንባባዎቿ፣ አገልግሏ፣ የቱሪስት መዳረሻነቷ፣ የጣና ፈርጥነቷ… ለባህር ዳራችን መለያዎቿ የመሆናቸውን ያህል፤ የባህር ዳር ጫትም ዋና መለያዋ ከመሆኑ በፊት የከተማዋ አስተዳደር በጥናት ላይ ተመስርቶ አንድ ነገር ማድረግ እንዳለበት አያከራክርም፡፡ እርግጥ ነው፣ ጫት እንዳይተከል፣ የተተከለውም እንዲነቀል፣ በከተማዋ እንዳይዘዋወር፣ ወዘተ. የሚያስገድድ መመሪያ ማውጥት ብዙም ጥቅም ላይኖረው ይችላል - ቢያንስ አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ፡፡ ለዚህ አይነቱ እርምጃ አዋጭ አለመሆን የትግራይ ክልል ተመክሮ አንድ ማሳያ ነው፡፡

ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ አደገኛ እፆችን (ጫት፣ ሲጋራ፣ ሀሺሽ፣ ኮኬይን፣ ወዘተ.) እና መድሀኒቶችን (ናርኮቲክ፣ ወዘተ.) በተመከለተ ከአመታት በፊት በአዳማ ከተማ ባዘጋጀው “ወርክሾፕ” ላይ እንደ ተገለፀው፣ የትግራይ ክልል መንግስት የጫት ምርት ከሌላ ክልል ወደ ትግራይ እንዳይገባ፣ ከትግራይ አንዳንድ የገጠር አካባቢዎች የሚመረት ጫትም እንዳይዘዋርና እንዳይሸጥ እንዲሁም ለምቶ የሚገኘው የጫት ተክል ተነቅሎ እንዲጠፋ ለማስገደድ ሙከራ አድርጓል፡፡ አንዱ የገጠመው ዋና ፈተና ከአምራቾች በኩል የመጣ ነው፡፡ አምራቾቹ፣ “ጫት ለጤና ጎጂ ስለሆነ ይጥፋ ማለታችሁ ጥሩ ነው፤ በዚህ እንስማማለን፡፡ አስካሪ መጠጥም እንዲሁ ለጤና ጎጂ ስለሆነ እንዲጠፋ አድርጉ፡፡ ይህን ካደረጋችሁ፣ የጫት ተክላችንን ነቃቅለን እንጥላለን” በማለት አስተዳደሩን አፋጠጡ፡፡ በመሆኑም አስተዳደሩ የማስገደድ ዝንባሌውን ትቶ በማስተማር ላይ አተኮረ፡፡ የሆነ ሆኖ ከጫት አምራቾቹ የተነሳው የመከራከሪያ ነጥብ፣ ከአመክኒዮ (logic) አንፃር ስናየው ውሀ የሚያነሳ አይደለም - አንድ ሰውን የሚጎዳ ነገር ቀድሞ ስላለና ስለተስፋፋ ይሄኛውም ጎጂ ነገር እንዲኖርና እንዲስፋፋ መፈቀድ አለበት ማለት ነውና፡፡

በትግራይ ክልል የተሞከረው ጫትን የመክልከል ሙከራ ውጤታማ ሳይሆን የቀረው፣ ጥናት ባለመደረጉና በጥናቱ ላይ ተመስርቶ ተገቢ የሆነ ፖሊሲ ባለመቀረፁ እንደ ሆነ መገመት ይቻላል፡፡ የባህር ዳር ከተማ አስተዳደርም ሆነ የክልሉ መንግስት በጥናት ላይ ተመስርቶ፣ ጫትን የሚመለከት ፖሊሲ ማውጣት ይኖርበታል ባይ ነኝ - በተለይም የባህር ዳርና አካባቢውን ጫትን በተመለከተ፡፡

የባህር ዳር ጫት፣ በአንፃራዊነት በርካሽ ዋጋ መገኘቱ በባህር ዳርም ሆነ በሚሰራጭባቸው ሌሎች ከተሞች በርካታ ሰዎችን በሱስ ወጥመዱ እያደነ በቀላሉ የጫት ቅኝ ተገዢ ለማድረግ አስችሎታል፡፡ ቢያን-ቢያንስ በሌላ አካባቢ የሚመረቱ የጫት አይነቶችን የበለጠበትንና ተመራጭ ያደረገውን ይህን ባህሪውን መቀማት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንፃር በጫት አምራቾችና አከፋፋዮች ላይ ከፍተኛ ግብር መጣል አንድ ጥሩ አማራጭ ሊሆን ይችላል፡፡ ያነጋገርኩት አንድ ጫት ሻጭ እንዳጫወተኝ ከሆነ፣ በተለይ የጫት አምራች ገበሬዎች የሚከፍሉት ግብር፣ ከጫት ምርት ለሚያገኙት ገቢ ሳይሆን፣ የአፈር ግብር አይነት ነው - ባላቸው የእርሻ መሬት ይዞታ መጠን ላይ የተወሰነና በአመት አንዴ ብቻ የሚከፈል፡፡

ስለሆነም የጫት አምራቾች የሚከፍሉት ግብር እጅግ-እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ከጫት ተክል ለሚያገኙት ገቢ ለመንግስት የሚከፍሉት ግብር የለም፡፡ በአመት አንድ ጊዜ የሚመረተው ጤፍ በኪሎ የሚሸጥበት ዋጋ ከ15 እስከ 16 ብር በሆነበት ከተማ፣ የጫት ቸርቻሪዎች አንድ ኪሎ ጫት በሁለት መቶ አርባ ብር ሂሳብ ነው የሚሸጡት፡፡ በዚህ ላይ በባህር ዳርና አካባቢው የሚገኘው የጫት ተክል በአብዛኛው በየሶስት ሳምንቱ አንድ ጊዜ ምርት ይሰጣል፤ ይህ ማለት ደግሞ በየአመቱ እስከ 17 ጊዜ ድረስ ለአምራቹ ገቢ ያስገኛል፡፡ ስለሆነም ሰውን ለማዳን፣ ትውልድን ለማትረፍ፣ አንድ ነገር ካልተደረገ በስተቀር ከሱስ ባህር ልትሰጥም የምትችልን አገር ለመታደግ ሲባል ሰው ሰራሽ የዋጋ ንረት በባህር ዳር ጫት ላይ መፍጠር ከጉዳቱ ጥቅሙ ማመዘኑ ያን ያህል አያከራክርም፡፡ መገናኛ ብዙሀንም ከፍተኛ ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ ይገባል፡፡ አንድ በየቀኑ የሚቅም ባለሱቅ ደንበኛዬ እንዳጫወተኝ፣ ሰሞኑን (ከጥር አጋማሽ በኋላ ባሉት ጥቂት ቀናት ውስጥ) መቶ ግራም ጫት አርባ ብር (ማለትም አንድ ኪሎ ጫት አራት መቶ ብር) በመግባቱ ለጊዜው ጫት መቃም አቁሟል፡፡ የባህር ዳር ጫት ዋጋ ቢንር፣ ብዙ ሰዎች ጫት ቃሚነታቸውን ሊተው የሚችሉበት እድል ሰፊ ለመሆኑ ይህ አንድ ማሳያ ሊሆን ይችላል፡፡

ባጭሩ ቅኝ ገዢው የባህር ዳር ጫት ከአማራ ክልል መዲና የሚሰራጭ እንደ መሆኑ መጠን፣ የክልሉ መንግስትና የከተማ አስተዳደሩ ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው በማስጠናትና ፖሊሲ በማውጣት ዘላቂ የሆነ መፍትሄ ማፈላለግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

# የጉዞ ማስታወሻ …

ከገጽ 10 የዞረ

የሚወስደውን አስፓልት ይዘን የቆቦ ከተማ ለቀን ወጣን። የተወሰነ ኪ.ሜትር ርቀት ከሄድን በኋላ የገጠር ቀበሌዎችን አገኘን። ከመኪናችን ወርደን አካባቢውን መጎብኘት ጀመርን። በቅርበት ከሚታየው ዘነብ መሐመድ ቤት ጎራ አልን። የተለያዩ ጥያቄዎችን ብናቀርብላትም ሁሉንም እንደማትመልስልን ገልጻ የተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ማብራሪያ ሰጠችን። ‹‹እንደ እናንተ መጥቶ የሚያየን፣ የሚጠይቀን ሰው ብዙ ነው። ነገር ግን እስከ አሁን በመንግስትም ሆነ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ምንም እርዳታ አልተደረገልንም። ቢሆንም ግን ይህን የሰቆቃ ዘመን ለማለፍ የራያ ቆቦ ማህበረሰብ ርስበርስ መረዳዳቱን ያውቅበታል እንጂ እስከ አሁን ድረስ በህይወት አታገኙንም ነበር›› አለችን። አብሮን ለመጣው ባለሙያ ‹‹እስካሁን ምንም እርዳታ አልተሰጠም? ብዬ ጠየቅሁት?››። ‹‹አዎ እዚህ አካባቢ አልተሰጠም። ከዚህ በላይ ጉዳት ለደረሰባቸው አካባቢ ብቻ ነው የተሰጠው። አሁን ግን ከዚህ አካባቢም ለመስጠት ዝግጅታችን አጠናቀናል›› በማለት ገለፀልኝ። የ1965/66፣ የ1977 ዓ.ም ድርቅ በሀገራችን ያደረሰውን ርሃብ እና ሰቆቃ አስታውሼ አሁንም ወደዚያ ዘመን እየሄድን ይሆን? ብዬ ሳስበው በጣም ዘገነነኝ። ተፈጥሮ ፊቷን ካዞረች አዞረች ነው። ምን ማድረግ ይቻላል? ቢሆንም ግን እነዚህ የሰቆቃ ጊዜያት ወደፊትም እንዳይከሰቱብን የተለያዩ የግብርና፣ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ስትራቴጂዎችን መንደፍ እንዲሁም የምርታማነት ማሳደጊያ ስልቶችን እና ቁጠባን ማጎልበት፣ መንግስትም ሆነ ማህበረሰቡ ከዚህ ቅስም ሰባሪ፣ ጉልበት አባካኝና እና አስቀያሚ ኖሮ ለመላቀቅ የሞት ሽረት ትግል ማድረግ ያስፈልጋል።

ራያ ቆቦ በተለይ በከብት ርባታ የምትታወቅ አገር ነች። በመሆኑም ይህ የድርቅ አደጋ በእንስሳት ሀብት ላይ አስከፊ በመሆኑ ችግሩን እጥፍ ድርብ እንዳደረገባቸው የነገሩኝ ደግሞ በወለሽ ቀበሌ የሚገኙት አርሶ አደር አቶ ተፈሪ አብርሃ ናቸው። አንድ በሬ ከዚህ በፊት በ10000 ብር እና ከዚያ በላይ ሲሸጡ እንደነበር ጠቁመው አሁን ግን 2000 ብር ቢበዛ 3000 ብር እንደማያልፍ ገልጸውልኛል። ከዚህ በመነሳት የድርቁ ችግር ይዞት የሚመጣው ጉዳት መጠነ ሰፊ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ተማሪዎች የአካባቢውን ሙቀት በመቋቋም አካባቢውን መጎብኘታቸውን ቀጠሉ። ነገ ተመርቀው ሲወጡ ሳይማር ያስተማራቸውን ማህበረሰብ ለማገልገል የቆረጡ ይመስላሉ። ለጊዜው ግን መንግስትም ሆነ ማህበረሰቡ የሰው ህይወት ማትረፍ ላይ መረባረብ እንዳለበት፣ ሁለት በሬ እና አንድ ላም አስቀርቶ ሌሎቹን እየሸጠ መጠቀም እንዳለበት እየተመካከርን እያለ የወረዳው የአደጋ መከላከልና የምግብ ዋስትና ባለሙያ አቶ ተመስገን መጡ። አቶ ተመስገን ከደመቀው ውይይታችን ሲደርሱ ሃሳባችን በከፊል ስለተረዱት የመንግስትም አቅጣጫም ይህ እንደሆነ ካልሆነ ግን ከተወሰኑ ወራት በኋላ ለእንስሳት የሚሆን መኖ እንደማይገኝ አስረዱን።

በዚህ ሁሉ ውስጥ ከወሎ ጫፍ እስከ ጫፍ ባየሁት የእንግዳ አቀባበል ባህል ተደንቄአለሁ። እንዴት ብትሉኝ፤ እንግዳ ሆኖ ችግር ለገጠመው ሰው መፍትሄ በመፈለግ ተወዳዳሪ የላቸውም። ወሎዬ ዘንድ ቢሮክራሲ ብሎ ነገር የለም። ቀኑን በሙሉ በትካዜና በድካም ስለዋልን እራት በጋራ እንድንበላ ዶ/ር አብርሃም መብራት ሃሳብ አቀረበ። እኛም በደስታ ተቀበለን የምንገናኝበትን ቦታ ተነጋግረን ስለነበር ከምሽቱ አስራ ሁለት ሰዓት ላይ ተገናኘን። በጣም ደስ የሚል እራት በልተን ሞቅ አና ደመቅ ያለች የጋራ ምሽት አሳለፍን። የራቱን መርሀ ግብር እንደጨረስን በማግስቱ አንድ ሰዓት ላይ ወደሚቀጥለው ጉብኝት ጉዞ የምንቀሳቀስበት ስለሆነ በሰዓቱ እንድንገኝ በመምህራን በኩል ማሳሰቢያ ተሰጥቶ ተለያየን። ከጥዋቱ አንድ ሰዓት ላይ የቆቦን ከተማ ለቀን ወጣን። ጉዛችንን ወደ ደቡብ አቅጣጫ አደረግን። የተማሪዎች ተወካይ በሆነው ተማሪ አጥላው ‹‹ቁርስ የምትበሉ አሁን ወደ ወልድያ እየገባን ለመብላት ተዘጋጁ፤ ያለዚያ ግን መብላት የሚቻለው ምሳ ሰዓት መሆኑ ነው›› በማለት ተናገረ። ቁርስ በላን። ሁለት ሰዓት ተኩል ላይ ወልድያ ከተማ ገባን። ሶስት ሰዓት ላይ መኪናችን ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ዞሮ መሄዱን ቀጠለ። የጋሸና ከተማን አገኘን። መኪናችን ነዳጅ ሊቀዳ ማደያ ቤት ገባ። መኪናችን ነዳጅ ከማደያ ከቀዳ በኋላ ከጋሸና ከተማ በስተሰሜን አቅጣጫ በ64 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ወደምትገኘው እና ወደ ታሪካዊቷ ላስታ ከተማ እንደምንሄድ ተነገረን። ጨኸት ጭብጨባና ፉጨት በመኪናችን ውስጥ ለረጅም ጊዜ አስተጋባ። ሁሉም ተሳፋሪ ላይ ደስታ ይነበባል። ምሳ በልተን ትንሽ አረፍ እንዳልን ጉዞ ወደ ላሊበላ ጀመርን። ወደ ላሊበላ የሚወስደው የጠጠር መንገድ አስፓልት ለማድረግ እየተሰራ ስለሆነ ሹፌሩ እረጋ ብሎ ያሽከረክራል። ከከተማዋ ትንሽ ኪ.ሜትሮች እንደራቅን ሙቀቱ እየጠነከረ መጣ። የአካባቢው መልካምድራዊ አቀማመጥ ወጣ ገባ ከመሆኑም በላይ ምድረ በዳ መሆኑ በጣም ያስጨንቃል። መኖሪያ ቤቶችም አልፎ አልፎ ይታያሉ። ከቤት እንስሳት ውስጥ በግ፣ ፍየልና አህያ ይታያሉ። የቀንድ ከብቶችን ግን አላየሁም። አልፎ አልፎ ቀልብን የሚስቡ በየመንገዱ የምናያቸው ህፃናት መኪና ባዩ ቁጥር የላስታ አካባቢ ውዝዋዜን ያስነኩታል። ድጋፋችንን በጭብጨባ እየገለጽንላቸው እናልፋለን። ላሊበላን ለመጀመሪያ ጊዜ ለማየት እየሄድኩ ስለሆኑ መንገዱ ረዘመብኝ። ዳገት በወጣን ቁጥር አሁን አሁን ደረስን እያልኩ ጉጉቴ ጨመረ። ከአክሱም ቀጥላ የላስታ ምድር 337 ዓመት በሙሉ ቤተ መንግስትና ቤተ ክህነት ሆና የኢትዮጵያ መኩሪያ በመሆን በአለም በክርስትና ሐይማኖትና በቅርስ የታወቀች ላስታ የነቅዱስ ይምርሃነ ክርስቶስ እና የነ ቅዱስ ላሊበላ አገር መሆኗን ሳስብ ድካሙን እረሳሁት። ላሊበላን ከተማ ወጣ ብሎ እንግዶችን ወደ ሚቀበለው አስፓልት መስመር መድረሳችን አቶ ታምራት ነገረኝ። ሹፌራችን እንደ ፎቅ ቀጥ ብሎ የላስታን ከተማ የከለለንን ዳገት ተያያዘው። ዳገቱን እንደወጣን ታሪካዊቷን የላስታ ከተማ ባየናት ጊዜ ፍጹም ደስታ ተሰማን። የከተማዋ አቀማመጥ ተራራማ ስለሆነ የከተማዋ ድምቀት ቁልጭ ብሎ እንደሌሎቹ ከተሞች አይታይም። ከቅዱስ ላሊበላ ቤተክርስቲያን ልንደርስ በግምት 200 ሜትር ሲቀረን ከመኪናችን ፊት ለፊት የነበረችው ባጃጂ ወደኋላ መንሸራተት ጀመረች። ሹፌራችንም መኪናውን አቁሞ የባጃጁን አመጣጥ እያየ ነበር። የመኪናችን እረዳት በፍጥነት ከመኪናችን ወረደና ባጃጇን አስቆማት። ያለንበት ቦታ ቁልቁለት ስለሆነ ያስፈራል። ከመኪናው ወርጄ ለመኪናው ታኮ ድንጋይ አስቀመጥኩ። የመኪናችን ረዳት እኔ ያስቀመጥሁትን ድንጋይ አንስቶ እሱ ያመጣውን ትልቅ ድንጋይ ታኮ አደርጋለሁ ሲል የእጅ ጣቶቹ ላይ ቀላል አደጋ ደረሰበት። ለመድረስ የነበረን ጉጉት በረዳቱ ላይ በተከሰተው አደጋ ተጨናገፈ። የመኪናችን የውስጥ ድባብ በድንጋጤ ተረበሸ። እኔ ጉዳቱ ሲደርስበት አጠገቡ ስለነበርኩ እጁን ቆረጠው ብዬ አስቤ ስለነበር በጣም ደንግጫለሁ። መምህር ይድነቃቸው መክብብ ‹‹አምሳሉ አንሄድም›› ሲለኝ ነው ከድንጋጤዬ የነቃሁት። አንዱን ተማሪ ጠጋ ብዬ ረዳቱ ወዴት ሄደ ብዬ ስጠይቀው ያፌት ይዞት ወደ ሆስፒታል እንደሄደ ነገረኝ። ያፌት ከተማሪዎች ተወካይ ውስጥ አንዱ ነው። በጣም ፈጣንና ከፊቱ ፈገግታ የማይለየው የ2008 ዓ.ም ዕጩ ተመራቂ ነው። እነ ያፌት ባይመለሱም እኛ ወደ ቅዱስ ላሊበላ ቤተክርስቲያን አመራን። ከዘመን ዘመን አልፈው እነሆ ዛሬ ላይ የደረሱትን ብርቅዬ የኢትዮጵያ ቅርሶችን ለማየት ከልብ በመነጨ ጽኑ ፍላጎት በሩ ላይ ቆመን መጠበቅ ጀመርን። አንድ አባት መጡና ከየት እንደመጣን እና ምን እንደምንፈልግ ጠየቁን። ጥያቄያቸውን አጠር አድርገን መለስልናቸው። ‹‹ሰዓት እየደረሰ ስለሆነ ፈጠን እያላችሁ ተከተሉኝ›› አሉ። ከእኝህ አባት ጋር ለመጎብኘት ፍቃድ ወደሚሰጥበት ቦታ ሄድን። ከየት እንደመጣንና ለምን እንደመጣን አባ አሳወቁ። ተማሪዎች ከሆኑ እየተፈተሹ እንዲገቡና ምንም አይነት ክፍያ ከተማሪ እንዳይቀበሉ ትዕዛዝ አስተላለፉ። ለተደረገልን ትብብር ምስጋና አቀረብን። መምህር ይድነቃቸው የቤተክርስቲያኑን መመሪያ ለተማሪዎች ከተናገሩ በኋላ ከፊት ከፊት ከሚመሩን አባት ጋር ቅዱስ ላሊበላ መጀመሪያ እንዳነፃት ወደሚነገርላት ቤተማርያም ቤተክርስቲያን ገባን። ስለ ቤተክርስቲያኗ አጭር ማብራሪያ ተነገረን። ቤተ-መድሃኒያለም፣ ቤተ-ገብርኤል እና በኖህ መርከብ ምሳሌ የተሰራውን ቤተ ጊዮርጊስን ጎብኝተን ሰዓት ስለደረሰ በቃችሁ ተባልን። ጊዜ ገደበን ምን ይደረግ እንዳሰብነው አልሆነም። ከአስራ አንድ ሰዓት በኋላ መጎብኘት እንደማይቻል ቤተክርስቲያኗ ታዛለች። የቤተክርስቲያኑን ስርዓት ማክበር ስለነበረብን ሳንወድ በግድ ለቀን ወጣን። ከቤተክርስቲያኑ በስተሰሜን አቅጣጫ በኩል ባለው በር ወጣንና አንድ ትልቅ ዋርካ ስር ቁጭ አልን። ቴክኖሎጂ እንደ አሁኑ ወቅት ባልተራቀቀበት በዚያን በ12ኛው ክፍለ ዘመን የሰው ልጅ አዕምሮ ምን ያህል ረቂቅ እንደነበር በማሰብ እየተደነቅን ነበር። ምክንያቱም ላሊበላን ለየት የሚያደርገው ከአንድ ወጥ ድንጋይ ከላይ ወደታች ተፈልፍለው የታነጹ አቢያተ ክርስቲያናትን መያዙ ነው። ለዚህ ይመስላል የውጭ አገር ጎብኝዎች ከሀገራችን አልፈው ስለ አሰራራቸው ድንቅ ጥበብ በመዘገብ በምስልና በድምፅ አቀናብረው ለአለም ሲያስተላልፉ የምናየው። የታሪክ ማሕደር የሆነችው ሃገራችን ዘመን የማይሽራቸውን እንዲህ አይነት ቅርሶችን ለትውልድ አቆይታለች። አሁን ያለው ትውልድስ ለቀጣዩ ትውልድ የሚያኮራ ምን ቅርስ ይተው ይሆን?

# ህልም እልም …

ከገጽ 15 የዞረ

ጀመረች። ጭንቅላቷ ውስጥ የሰከረ ሌባ የገባ ይመስል ሃሳብና ግምት እርስ በርሱ ይጋጭባታል። “ግደይ ከድቶኝ?. . . አባባ ተገሎ?” መላ ምቶች ርስ በርሳቸው እየተጋጩ ይመለሳሉ። “ፖሊስ ነገሩን ደርሶ. . .”

“ሲርርርርርር. . .” ስልኩ በድጋሚ ጮኸ። ከፀጉሯ እስከ ጥፍሯ ነዘራት። “. . .ሲርር” ለሷ ወይም ላያቷ የሚነፋ የመጨረሻ ጡሩንባ። “ሲርርር” አነሳችው። ”ሄሎ”. . . “ሄሎ ኤልሲ ደህና አመሸሽ መውደድ ነኝ።” ያጎቷ ልጅ መውደድ። የዋኋ መውደድ፤ ሳቂታዋ መውደድ፤ ህይወት ያልተገለፀላት መውደድ። ልቧ ደለቀ። “ሞት ወይም ሽረት!” “ድል ወይም ሽንፈት!”. . . እእ መውደድዬ ምን ሆነሽ ነው?

“ይቅርታ ኤልሲ በሌሊት አስደነገጥኩሽ?” ድምጿ ከድካም በስተቀር አዲስ ነገር ያለው አይመስልም።

“አባባ ምን ሆኗል አሁን እኮ ከፖሊስ. . .”አቋረጠቻት

“አዎ አንቺ ሳታዋሪያቸው ስትቀሪ እኔ ጋር ደውለው ነበር” ኤልሳ ተቁነጠነጠች “የምስራች አያታችን ሞቷል፤ ማጅራት መቺዎች አፍነው ገለውታል” እንድትላት ጓጉታ ጆሮዋን ቀሰረች።

“ንገሪኝ እንጂ!” የደነገጠች መስላ ጮኸችባት።

“ያው አባባን ታውቂው የለ. . . የሆነ ቦታ ተቀምጦ የሆኑ ሰዎች. . .” ሳቋና እንባዋ እኩል አፋጠጣት። ውርደቷ አበቃ ክብሯ ባይመለስ የዝናዋ ሚስጢር ግን አበቃለት ከእንግዲህ ልጅ ስለሆንሽ ነው ክፉ የሰራሽው፤ ልጅ ስለሆንሽ ነው ጨካኝ የሆንሽው፤ ልጅ ስለሆንሽ ነው. . .” የሚላት የለም። ከእንግዲህ ሚስጥሯ ማንም እንዳያገኘው ጅራቱ ተቆርጧል። ከእንግዲህ አያት የላትም። ሚስጥረኛ የላትም. . . ተቆርቋሪ የላትም. . .ከእንግዲህ ወዳጅ ምቀኛ የላትም. . . የላትም። ጓጓች። የአያቷን መርዶ ለመስማት ጓጓች። ቀብሩ ላይ እንዴት እየተንሰቀሰቀች አልቅሳ እንደምታለቅስ አሰበች።

“. . . እና ሰዎቹ ያንቺ አድናቂዎች ነበሩና ባለፈው በስራሽ ተናደው ሲሰድቡሽ ተናዶ. . . በያዘው ከዘራ ፈነካክቷቸው ታሰረና ዋስ. . .”

“እ??!”

“አይዞሽ አትደንግጪ። በጠዋት ሄደን እናስፈታዋለን። ምን ይሆናል ብለሽ ነው? አባባ እንኳን ፖሊስ ጣቢያ ስንት አመት በርሃ የቆየ ጀግና አይደል እንዴ?”

“ሂሂሂሂሂ. . . .”

**ይቀጥላል!**

# እንግዳችን ...

ከገጽ 9 የዞረ

ከእኔ አልፎ የራሳቸውን የግል አስተሳሰብ ያጠራላቸውና የተሳሳተ ግንዛቤያቸውን ያስተካከለላቸው ሆኖም አግኝተውታል። እኔም ከዚህ በኋላ መሥራት ለማስባቸው ነገሮችን ድፉን ያስቀመጥኩበት የመሠረት ድንጋይ የሆነ ሥራ እንደሆነ ይሰማኛል። በተግባር ላይ ቢውል ሊያስገኝ ስለሚችለው ዘለቄታዊ ለውጥ ቅንጣት ታህል ጥርጥር የለኝም። ስለዚህ ምርምር የራሳችንና የቅርብ ማኅበረሰባችን የሕይወት እንቆቅልሽ የሆኑ ችግሮችን በየሙያ ዘርፋችን መነጽር የምንፈታበት ጥልቅና ክቡር ሥራ መሆኑን ብንረዳ የየእለት ውሏችን ውስጥ ሁሉ ምርምር ያለችግር ባሕል ሆኖ በነገረ ሥራችን ሁሉ የሚገለጽ ስለሚሆን በኃላፊነት ወይም በግል ሥራ ውጥረት ተውጦ ያልተምታታ የማስተማርና የምርምር ሕይወት ይኖረናል። በሰለጠነው ዓለም ያለው የምርምር አካሄድ የራሳቸውን እንቆቅልሽ መፍታት ላይ ያተኮረ ነው። የሰው ኃይል እጥረት ሲኖርባቸውና መላው ሲጠፋቸው እንዲህ እኛን የትምህርት ዕድል በመስጠት ጭምር የነርሱን ችግር እንድንፈታ ይጋብዙናል። እኛም የነርሱን አርኣያ እንከተልና የሌሎችን ሳይሆን የራሳችንን እንቆቅልሾች መፍታትን የምርምር ዋና አጀንዳችን እናድርገው፤ ያኔ ምርምር አንድ የአስተሳሰባችን መንገድ ሆኖ ይዋሃደናል።

**ናይል፡-** ስለ ትምህርት ጥራት ስናስብ መምህራን የፖሊሲ ችግር ነው ይላሉ። መንግስት የመምህራን ችግር ነው ይላል፤ ምክንያቱም መምህራን ለተማሪዎቻቸው በክፍል ውስጥ ከጽንሰ ሃሳብ የዘለለ በተግባር የተደገፈ ከነባራዊ አለም ጋር የተሳሰረ የማስተማር ልምዳቸውን በማቆማቸው ነው ይላል። በመሆኑም በሰለጠነው አለም ላይ ያለ የሁለቱን አመለካከት የሚያስታርቅ ሃሳብ ይኖር ይሆን? ካለስ እንዴት?

**ዶ/ር መስከረም፡-** በሰለጠነው ዓለም መምህራን “ከጽንሰ ሃሳብ በዘለለ ተማሪዎችን ለነባራዊው ዓለም ሕይወት በሚያዘጋጅ መልኩ እንዲያስተምሯቸው ያስችላቸዋል” ተብለው የሚታሰቡ ዘዴዎችና አካሄዶች በሙሉ የሚመነጩት “ሕጻናትንና ታዳጊዎችን እንደሰው ከማየት ነው” የሚል መሠረታዊ የሆነ ግንዛቤ አላቸው። ይኸንንም “humanizing pedagogy” “personalized education” “educating the whole child” ወዘተ... በሚባሉ የተለያዩ ስሞች ይጠሩታል። አጠራሩ ቢለያይም መሠረታዊ ሃሳቡ ያው ነው። በእኛ ሀገር ከትምህርት ጥራት መጓደል ጀርባ ያለው ትልቁ ችግር የዚህ ነገር መጥፋት ነው። “ምን ማለት ነው? የእኛ መምህራን ተማሪዎችን እንደሰው አያዩዋቸውም እንዴ?” ልትለኝ ትችላለህ። ነገሩ በግርድፉ እንደዚያ ብለን የምንተረጉመው አይደለም። አባባሉ በእኛ ሀገር ባለው አካሄድ “ተማሪዎችና መምህራን የጋራ ጉዳይ፣ ማኅበራዊ ግንኙነትና አብረው የሚቀበሉት የወደፊት ዕጣ ፈንታ እንዳላቸው የአንድ ኅብረተሰብ አባላት እየተያዩ የሚያደርጉት ዓይነት ግንኙነት የላቸውም” ለማለት ነው።

ለምሳሌ አንድ የ4ኛ ክፍል መምህር “እነዚህን ሕጻናት በማኅበረሰብ ውስጥ ለሚኖራቸው ሕይወትና ሚና ብቁ አድርገህ በማዘጋጀት አሰልጥን፤” ወይም “አሳድግ” ተብሎ ሃምሳ ሕጻናት ቢሰጠው እነዚያን ሕጻናት ብዙ ተግባራዊ የሆኑ ነገሮችን እንደሚነግራቸው፣ እንደሚያሳያቸውና እንደሚያሠራቸው በቀላሉ መገመት እንችላለን። አቀማመጥ፣ አነጋገር፣ አካሄድ፣ አበላል፣ አጠጣጥ፣ ምግብ አዘገጃጀት፣ ንጽሕና፣ መጻፍ፣ ማንበብ፣ መገበያየት፣ መመጠን፣ መለካት፣ ራስን መከላከል፣ ልብስ ቢቀደድባቸው መስፋት፣ ከጓደኞቻቸው ጋር ተግባብቶ መጫወት፣ አንዳንድ ትናንሽ ቁሳቁሶችን መሥራት፣ የመሳሰሉት ሁሉ ሙሉ ስሜቱንና ልቦናውን በመጠቀም ለልጆቹ ሊያሳያቸው ይችላል። ነገር ግን ያ መምህር ለምሳሌ፡- የሂሳብ መምህር ተብሎ በሰብአዊው የግንኙነት ሥርዓት ሳይሆን በአስኳላው ደንብ ብቻ ተማሪዎቹን በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ያለውን ርእስ ተከትሎ መደመር፣ መቀነስ፣ ማባዛት እና ማካፈል ለማስተማር ሲነሳ ልጆቹን በሰብአዊና ማኅበራዊ መንገድ ማናገር ያቆምና የሚያሳያቸው ግንኙነት ባይተዋር (impersonal) ይሆናል። እዚህ ጋር ትምህርቱ በመምህሩና በተማሪዎቹ መሃል ገብቶ ሁለቱን የማራራቅ ተጽዕኖ ይፈጥራል። የመምህሩም ታማኝነት ለሥርዓተ-ትምህርቱ ይዘት እንጂ ለልጆቹ መሆን ያቆማል። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ላይ መምህሩ ሕጻናትን ከእለት እለት ለሚኖሩትና ለወደፊትም ለሚመሠርቱት ሕይወታቸው በማሰልጠን ስሜት የሂሳብ ትምህርትን ሊያስተምራቸው አይችልም። ትምህርቱም ከነባራዊው ዓለም ተግባራዊነቱ ተነጥሎ የጽንሰ-ሃሳቦች ስብስብ ብቻ ይሆናል። ይህ የሚስተካከለው መምህራን የሚያስተምሩት ትውልድና የአገሪቱ የወደፊት ዕጣ ፈንታ በእጃቸው መሆኑን ሲያውቁና በሁለንተናዊ ማንነታቸው የዚያን አካል መሆናቸው ጠልቆ ሊሰማቸው ሲችል ብቻ ነው። በዚያ ደረጃ እንዲያስቡ ማዘጋጀት ካልተቻለና የተሰጠቻቸውን 45 ደቂቃ ብቻ በተሰጣቸው ርእስ ላይ አስተምረው ሌላ ሌላውን በመተው አርፈው እንዲቀመጡ ስናዘጋጃቸው ሚናቸውንና ማንነታቸውን እንገድበዋለን። ያ ከሆነ ነባራዊውን ዓለም ከሥራቸው ነጥለው እንዲመለከቱትና ማንኛውም ብላሽ ቢመጣ መንግሥትን ወይም ትምህርት ሚኒስቴርን በመውቀስ ለራሳቸው ኃላፊነት መውሰድ እንዲያቆሙ ያደርጋቸዋል። መምህር የአገር ባለቤትነት በማይሰማው ሁኔታ ጥራት ያለው ሥራት ውልዱ ላይ ሊሠራ አይችልም። በመምህራን ሥልጠናና ቅጥር ዙርያ ያለን ባለድርሻ አካላት በሙሉ እንደ ደመወዝ ማነስ ከመሳሰሉ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ያለውን የመምህራንን ቅሬታ ብቻ እንደተገቢ ጥያቄ ከማየት አልፈን ይህን የባለቤትነት ስሜታቸውን እያጠፉባቸው ያሉትን ችግሮች በሙሉ ከነምንጮቻቸውና ውጤቶቻቸው በደንብ ልናያቸውና ሥራ ልንሠራባቸው ይገባል።

**ናይል፡-** ካለዎት ግንዛቤ የአካዳሚ ነፃነት ሲባል ምን ማለት ነው? አሁን ያለው ነባራዊ ሁኔታስ ምን ይመስላል?

**ዶ/ር መስከረም፡-** “የአካዳሚክ ነጻነት” ማለት በእኔ ግንዛቤ ለመምህራንና ሌሎች ተመራማሪዎች ለአገሪቱ ይጠቅማል ብለው በሚያስቡት መሥመር ሁሉ ላይ እውቀትንና እውነትን በመፈለግና በማሳወቅ በማስፋፋት ተሠማርተው እንዲሠሩ ዕድሉን ጊዜውንና አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ ሲያገኙ ነው። አሁን ያለውን ሁኔታ ስንመለከተው ለምሳሌ የኛን ዩኒቨርሲቲ ብናየው መምህራንን በዚህ ረገድ ለማበረታታት አስተዳደሩ ረጅም ርቀት የተጓዘ ይመስለኛል። በዚህ ረገድ የተፈጠረው መነሳሳትና ወኔ ከውጪ ስመጣ አገኘዋለሁ ብዬ ከጠበቅሁት ደረጃ በላይ ነው። መምህራን ይህን መነቃቃትና መነሳሳት ተጠቅመው የራሳቸውን የምርምርና የማስተማር ሥራ ከፍ ወዳለ ደረጃ ለማሸጋገር ዕድሉን ሊጠቀሙበት ይገባል” የሚል እምነት አለኝ። ከዚህ ጋር ተያይዞ “ምርምሮች ችግር ፈቺ እንዲሆኑ ምን ይደረግ?” በሚለው ዙር በየመድረኩ የሚካሄደው ውይይት“ ወቅታዊና ተገቢ ነው” እላለሁ። ይህ እንዳለ ሆኖ “የአካዳሚክ ነጻነትን የሚገድቡ ችግሮች የሉም” ማለት ግን አይደለም፤ አሉ። እነዚህ ችግሮች የግድ በችግርነት ሳንመለከታቸው እንችላለን። “ተጽዕኖ እየፈጠሩ አይደለም” ማለት ግን አይደለም። ለምሳሌ የተለያዩ የአገር ውስጥም ሆኑ የውጭ ድርጅቶች መንግሥታዊ የሆኑም ይሁኑ ያልሆኑ የምርምር በጀቶችን ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለመልቀቅ ሲያስቡ የሚመርጧቸውን ወቅታዊ ርእሰ-ጉዳዮች ተከትሎ የምርምርና የአካዳሚክ አጀንዳዎች ይገደባሉ፤ ሆን ተብሎ ሳይሆን በተዘዋሪ መምህራን አብዛኛውን ጊዜ “በዚህኛው ወይም በዚያኛው ርእሰ ጉዳይ ላይ ካልሠራሁ ፈንድ አላገኝም” “ባሁን ጊዜ በአገር አቀፍ/ ዓለማቀፍ ደረጃ ትልቅ የምርምር አጀንዳ የሆነው ይሄኛው ወይም ያኛው ጉዳይ ነው” የሚል ጠቅላላ ግንዛቤ ይዘው በሚሠሩበት ሁኔታ በራሳቸው እይታና በሙሉ ስሜታቸው “አንገብጋቢ ችግር ነው” ብለው የሚያስቡት ጉዳይ ላይ “የማሰብና የመመራመር ዕድል ይኖራቸዋል” ብዬ አላስብም። ቢኖራቸውም እንኳ ልባቸው ወደ ዚያኛው መሰቀሉ አይቀርም። የፈንዶችና የፕሮጀክቶች አቅጣጫዎች ያስገድዷቸዋልና። ይሄ ከምናስበው በላይ ጉዳት አለው።

መምህራን ጥናትና ምርምር ሊያደርጉባቸው የሚገባቸው ችግሮች እና በባለድርሻ አካላት ቅድሚያ የሚሰጧቸው ርእሰ–ጉዳዮች ሁልጊዜ ላይገጣጠሙ ይችላሉ። እንዲያውም አንድ ማወቅ ያለብን እውነታ ለእያንዳንዳችን በየሙያችንም ሆነ እንዲሁ በጠቅላላ እይታችን በማኅበረሰባችንና በአገራችን ውስጥ አንገብጋቢና መፈታት ያለበት ችግር ሆኖ የሚታየን ነገር እንደግለሰባዊ ማንነታችን የተለያየ መሆኑንና በዚያ ችግር ዙር ያ ደግሞ እንደዚያ የሚሰማውን ያንን ሰው ያህል ማንም ሰው ጥሩ አድርጎ ሊመራመርበትና ሊያስተምርበት የማይችል መሆኑን ነው። በዚህ መልክ ብቻ ነው እውነተኛ የሆነ የአእምሮ ሥራ (genuine scholarship) የሚኖረው። ስለዚህ፡ “የአካዳሚክ ነጻነት ማለት ይህ እንዳይሆን የሚያግዱ ነገሮችን ለማስወገድ መምህራንና ባለ ድርሻ አካላት ከየራሳቸው በመጀመር በየፊናቸው ሊያደርጉት የሚገባ የራስን እይታ ከሁኔታዎች ገዳቢነት ነጻ የሚያወጡበት ወሳኝ ሂደትም ጭምር ነው” እላለሁ። ከዚህ በተጨማሪ ግን አንዳንድ መምህራን በሚኖራቸው አቋምና መርህ ምክንያት ከመንግሥት የሚደርስባቸው ችግር በሙሉ የአካዳሚክ ነጻነትን የሚጻረርና ለማንኛውም ወገን የማይበጅ ለመኾኑ እኔ ማብራራት የሚያስፈልገኝ ነገር አይሆንም።

**ናይል፡-** አብዛኛው የሀገራችን ምሁራን ወደ ውጭ ሃገር ሄደው መቅረት እንጂ በውጭ ሃገር ያገኙትን እውቀትና ገንዘብ ወደ ትውልድ ሃገራቸው ተመልሰው ማህበረሰቡን የማገልገል ባህል አልተለመደም። ስመሆኑ እርስዎ ይህንን ሁሉ ሰብረው ወደ ሃገረዎ ተምልሶ መሥራት ያሰቡበት ነገር ይኖር ይሆን?

**ዶ/ር መስከረም፡-** እኔ በ1998 ዓ.ም. ወደ አሜሪካ ስሄድ ለራሴ ለመመለስ የማስበውን ሙያዊ ጥያቄ እንጂ “ወደ ሀገሬ እመለሳለሁ? ወይስ አልመለስም?” የሚለውን ጥያቄ እያሰላሰልኩ አልነበረም። ሲጀምር የሄድኩበት ቪዛ J-1 ነው። ማለትም ወደ ሀገር ቤት ለሁለት ዓመታት ያህል ተመልሶ የመሥራት ግዴታ እንዳለብኝ የሚያሳስብ ቪዛ ነው። ያ ደግሞ የፓስፖርቴ ገጽ ላይ በግልጽ የተቀመጠ ነገር ነው። አሜሪካ በመቆየት ረገድ ብቸኛ ያሳሰበኝ ጉዳይ “ሦስተኛ ዲግሪዬን ሳልሠራ እመለስ ይሆን?” የሚለው ጥያቄ ብቻ ነበረ። ያ ደግሞ ሁለተኛ ዲግሪዬን እየሠራሁ በነበረበት ጊዜ ከዶክትሬት ተማሪዎች ጋር ኮርሶች እየወሰድሁም ጭምር ለራሴ ልረዳቸው የምፈልጋቸውን ርእሰ ጉዳዮች እዚም እዚያም ነካክቼ ምንም ባላደማኋቸው ሁኔታ ላይ ትቻቸው ስለነበረ ነው። ይሄ ስጋቴም ወደ ሀገር ቤት ስመለስ ልሠራው ለማስበው ነገር በቂ ግንዛቤ እንዲኖረኝ የሚያስችል ጊዜና ዕድል ለማግኘት ከመፈለግ የመጣ ነበር። አንዴ ሦስተኛ ዲግሪዬን ከጀመርኩ በኋላ ግን በተለይ ከፈረንጆቹ 2012 ዓ. ም. ጀምሮ በትክክል መሥመሬን እንዳገኘሁ እየተረዳሁ ከመጣሁ በኋላ ወደ ሀገር ቤት እንዳልመለስ ጫና የሚፈጥርብኝ ምንም ጉዳይ አልነበረም። ስለዚህ ወደ አገሬ ስመለስ ምንም ልሰብረው የሚያስፈልገኝ ወጪ የመቆየት ባህልም ሸክምም አልነበረብኝም። ባሁኑ ጊዜ ዱሮም እመኘው ስለነበረውና አሁን ቀጥሎ ስለምሠራው ነገር እያሰብኩ ነው። ይሄ ደግሞ የሆነ ጊዜ ላይ ከአገር ውጪ እንድሄድ እንደሚያስገድደኝ አውቃለሁ። ያንን ከማድረግ የሚያግደኝም እስከማውቀው ድረስ ምንም ነገር የለም። ከዚያ ደግሞ ወደዚሁ እመለሳለሁ። ስለዚህ ባጭሩ ጥያቄዬ ወደሚመራኝ ስለመሄድና ያሰብኩትን በዚህች ሀገር ላይ ስለመተግበር እንጂ ውጭ ስለመቆየት ስላለመቆየት አሳስቦኝ አያውቅም። ይህ ከፍተኛ

ወደ ገጽ 14 ዞሯል

# እንግዳችን ...

ከገጽ 13 የዞረ

የሆነ ነጻነት ሰጥቶኛል:: በዚህ አጋጣሚ ልጠቅሰው የምፈልገው ነገር ቢኖር ቤተሰቦቼ የምፈልገውን እንዳደርግ ምርጫውን ለእኔ ከመተው በቀር አንድም ቀን "የሚበጅሽን እንንገርሽ" በሚል መንፈስ ውጭ እንድቀር ጫና ስላላሳደሩብኝ ለእኔ እውነተኛ የሆነ ፍቅር እንዳላቸውና ቅንጣት ታህል ራስወዳድነት እንዳልፈጠረባቸው አረጋግጠውልኛል:: ለዚህም ፈጣሪ ዋጋቸውን ይክፈላቸው:: በቤተሰብ ግፊትና ጫና የፖለቲካ ጥገኝነት ጠይቀው ያለፍላጎታቸው ከሀገር ውጪ እየኖሩ ያሉ ኢትዮጵያውያን ምሑራንን ያለባቸውን የስነ-ልቦና መረበሽ አይቻለሁ:: ያለ ፍላጎት የሚደረግ ነገር ሁልጊዜ ዘላቂ ውጤት አይኖረውም::

**ናይል:-** **ከመደበኛ ሥራዎት በተጨማሪ ለማህበረሰቡ ብሎም ለሃገሪቱ እድገት የበኩሌን አስተዋጽኦ አድርጊያለሁ የሚሉት ሥራ ካለ ቢገልፁልን?**

**ዶ/ር መስከረም:-** ለእኔ ለማኅበረሰቡና ለአገሪቱ ዕድገት አስተዋጽኦ ለማድረግ የምሠራውን ሥራ ከመደበኛ ሥራዬ ነጥዬ አላየውም:: ያለኝ ግንዛቤ መደበኛ ሥራዬ በራሱ የሚያዝዘኝ ለሀገሪቱ ዕድገት እንድሠራ እንደሆነ ነው:: ያንን ደግሞ "ይህን ወይም ያንን አድርጌ በዚህ መጠን አገሪቱን የሚያሳድግ ሥራ ሠራሁ" ብዬ በሚለካ መንገድ የማስቀምጠው ነገር አድርጌ አላየውም:: ከዚያ ይልቅ በአካዳሚክ ሕይወቴ በየምዕራፉ የሚገጥሙኝን መንታ መንገዶች ለማለፍ አቅጣጫዬን የምወስነው "ለሀገር የሚጠቅም አንድ ሥራ ለመሥራት ያስችለኛል" ብዬ በማስበው መንገድ እንዲሆን በማድረጌ መጠን ነው የማየው:: ያንን ደግሞ አሁን ሳይሆን የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ እያለሁ የጀመርኩት ነገር ነው:: ከፍተኛ ውጤት የነበረኝ በተፈጥሮ ሳይንስ የትምህርት ዓይነቶች ሆኖ እያለ የነበረብኝን የአእምሮ ፍጭትና የሌሎችን ተቃውሞ ተቋቁሜ ማኅበራዊ ሳይንስን የመረጥኩት "ስለዝች ሀገር የበለጠ ያስረዳኛል" ብዬ በማመን ነው:: ከዚያ በኋላ በየምዕራፉ የመረጥኳቸው እያንዳንዳቸው አቅጣጫዎቼ በዚህ መልክ የተደረጉ ናቸው:: ስህተት ሆኖ ያገኘሁት ምንም ዓይነት ምርጫ እስካሁን አላደረግሁም:: ይህች "ኢትዮጵያ" የምንላት አገርም እንዲህ ያለውን አካሄድ የሚከተልን ሰው በራሷም ሚሥጢራዊ መንገድ የምትረዳበት ተአምራዊ ኃይል ያላት አገር መሆኗን አይቻለሁ:: እንግዲህ የኔና የርሷ ጥምረት ከዚህ በኋላም የሚቀጥል ይሆናል:: "ይህን ሠርቻለሁ" ብዬ በመዘርዘር ጊዜዬን አላጠፋም:: ጀመርኩት እንጂ ገና ሩቡን እንኳን አልኼድኩበትምና::

**ናይል:-** **በተማሪነት ሆነ በሥራ ህይዎትዎ ያጋጠሞትን ፈታኝ የሚሏቸው ነገሮች ካሉ ቢያጫውቱን?**

**ዶ/ር መስከረም:-** አዎን:: "ፈታኝ" ብዬ የማስበው ነገር በተማሪነት ሕይወቴ ገጥሞኛል:: እርሱም አሜሪካ ሦስተኛ ዲግሪዬን እየሠራሁ እያለ የገጠሙኝ ተደራራቢ ፈተናዎች ናቸው:: የነበርኩበት ዩኒቨርሲቲ የሥርዓተ-ትምህርት መርኃ ግብር (Curriculum and Instruction Program) በመጀመሪያ የተቀበለኝ በማኅበራዊ ሳይንስ ዘርፍ አንድ ረዳት ፕሮፌሰር ብቻ ይዞ ነበር:: እኔ በአማካሪነት እንዲመደብልኝ ያመለከትኩት ፕሮፌሰር እኔ ልክ ስገባ እርሱ ኮሌጁን ለቅቆ ወደሌላ ግዛት ሄደ:: የነበረኝ አማራጭ ካለው ረዳት ፕሮፌሰር ጋር መሥራት ነበር:: እኔ በወቅቱ እንደ ችግር አላየሁትም፤ ለካ ሰውየው tenure track ላይ ስለነበረና በቂ የሆነ የምርምር ህትመት ስለሌለው ያስመረቀው የሦስተኛ ዲግሪ ተማሪም ስላልነበረ ጊዜውን ወደታች እየቆጠረ ሥጋት ላይ የነበረ ፕሮፌሰር ነበር:: እኔን ወደ መርኃ ግብሩ መግባት ተከትሎ ሰውየው እኔን ከሚጠበቅብኝ በላይ ሥራ በማሠራት ራሱን ማዳን ስለፈለገ ኋላ ለሚከሰቱት ጥያቄዎች መከላከያ ለማዘጋጀት ቀስ በቀስ ስለ እኔ የተዛቡ መረጃዎችን ለሌሎች ፕሮፌሰሮች ከወዲሁ በማሠራጨት እንድገለል አደረገኝ:: ከጀርባዬ እየተካሄደ ያለውን ነገር ስለማላውቅ የሥራ ጫና ናት ትርጉም የሌለው ልፋት እየበዛብኝ መጣ:: እርሱ ለካስ "ይህ ባይሳካ ያኛው! ያኛው ባይሆን ይኸኛው!" እያለ ነው የተተረማመሰ ፕሮጀክት እዚህም እዚያም ያስጀምረኝ የነበረው:: በዚህ ዓይነት ሁኔታ ለአንድ ዓመት ተኩል ከቆየሁ በኋላ ጥያቄ ማንሳት ጀመርኩ:: የተዛቡ መረጃዎች ስለ እኔ "የአካዳሚክ ብቃት ማነስ" በቅድሚያ ተሠራጭተዋልና ሰሚ አላገኘሁም:: የበላይ ኃላፊዎች የተባሉት ሁሉ እኔ ለአቤቱታ ቢሮአቸው ሳልደርስ መልስ አዘጋጅተው ይጠብቁኝ ነበር:: ስለዚህ በራሴ ጊዜ አማካሪዬን ልቀይረው እንደምፈልግ ነግሬ ተሰናበትኩት:: ኮሚቴ የነበሩትንም በሃይማኖታዊ አመለካከቴ ስላልተግባባን ተሰናበትኳቸው:: ማን አማካሪዬ ይሁን? ኃላፊነት ሊወስድ የሚፈልግ ጠፋ:: ለእኔ ሁሉ ነገር መረዳት ከምችለው ውጭ ነበር የሆነብኝ:: እንደምንም ሌላ አማካሪ አግኝቼ ሥራዬን ስቀጥል ደግሞ በሁለተኛው ዓመት ማገባደጃ ላይ የባራክ ኦባማ አስተዳደር በአሜሪካ ያለውን የኢኮኖሚ ቀውስ ለማስተካከል ወጪን የመቀነስ አማራጭ ለመከተል በመምረጡ ከዩኒቨርሲቲዎች ዓመታዊ በጀት ላይ ሃያ በመቶ እንዲቀነስ በፈረንጆቹ 2011 ዓ.ም ውሳኔ ተሰጠ:: ይህ እኔ በነበርኩበት ኮሌጅ ያመጣው ቀጥተኛ ተጽእኖ ኮሌጁን ረዳት ምሩቆችንና በፊት ጊዜ ተቀጥረው የሚያስተምሩ መምህራንን በተመጣጣኝ እጅ በቁጥር እንዲቀንስ ስላስገደደው አሜሪካዊ ያልሆነን ረዳት ምሩቆች ያለምንም ቅድመ ማስጠንቀቂያ ድንገት "በጀት የለም" ተብለን ሥራችን እንዲቋረጥ ተደረገ:: ይህን ውሳኔ ሲወስኑ "ልጆቹምን ይበላሉ? የት ይኖራሉ?" ብለው እንዴት እንዳላሰቡ እስከዛሬ ድረስ ሳስበው ይገርመኛል:: ከሁሉም የበለጠ የሚገርመው ዜጋ ያልሆነ የድኅረ–ምረቃ ተማሪ ሥራ እየሠራ ካልሆነና ኮርስ ካልጨረሰ "non-resident surcharge" የሚባል ክፍያ ጭምር እንዲከፍል የሚጠበቅበት መሆኑ ነው:: ስለዚህ፡ "ብትፈልጉ ዩኒቨርስቲውን ለቅቃችሁ ውጡ፤ እንደፍጥርጥራችሁ" ማለታቸው እንደሆነ ገባኝ:: ሌሎች ከእኔ በኋላ ወደ ኮሌጁ የገቡ ከአፍሪካ የመጡ ተማሪዎች ጋር በመሆን "አቤት" ልንሞክር የባሰ ተጠቆርን:: የምርምር ስብዕና የሌላቸው ገንዘብ ፈላጊዎች አድርገው በመቁጠርም "እንዲያውም በደንብ ሳትሠሩ ነው በባዶ ሜዳ የምንከፍላችሁ" በማለት መሥመር ያለፈ ንግግር ተናገሩን:: ስለዚህ ሌሎቹ እንደ አማራጭ የወሰዱት ቆይታቸውን ለማሳጠር በፍጥነት መጠይቅ እንደነገሩ በየትምህርት ቤቱ ነው:: የሆነ ነገር ጽፈው ተመርቆ መውጣትን ነበር:: እንዳሰቡትም አድርገው ከእኔ አንድ ዓመት ቀድመው ተመርቀው ፈትለክ ብለው ወጡ:: ቀድመው የሠሯቸው የጥናት ግኝቶቻቸውም በፕሮፌሰሮቻቸው ያለፈቃዳቸው ተወሰዱ (ማለትም plagiarize ተደረጉ):: እኔ ግን የሆነ እልህ ነገር ያዘኝ መሰለኝ በቅድሚያ ኦፊሽያል የገንዘብ እርዳታ ለዲፓርትመንቱ በመስጠት ስሜን ከ"donors" ተርታ በመስታወት በኮሌጁ ሕንጻ ዋና መተላለፊያ ላይ እንዲመዘገብ አደረግሁ:: የጨዋታው ሜዳ ተቀየረና የማደርገውን በተለየ ዓይን መከታተል ጀመሩ:: አንዳች ነገር በተከሰተ ቁጥር "ለምን?" ብዬ መጠየቅ በፍጹም ላቆም አልቻልኩም:: የሥነ-ምግባር ወይም የዲሲፕሊን ችግር እንዳለብኝ በማስመሰል በእኔ ላይ ችግር ሊፈጥሩ ሲሞክሩ ያንን የሚያፈርስ የemail መረጃ ለሁሉም ግልባጭ አድርጌ እለቅ ነበር:: በእኔ term ካልሆነ በቀር በነርሱ term ለመሄድ ጨርሶ ፍላጎቴ ጠፋ:: ስለዚህ ኮሌጁ እኔን እንደ "አደገኛ" በማየት ኮሌጁን ወክላ የSchool of Education ዳይሬክተር ከእኔ ጋር ጠበቃ ባለበት የእኔንና የማንኛውንም መምህር የግንኙነትን ሥርዓት የሚወስኑ taylor-made የሆኑ ሕግጋት አውጥተው እንድንፈራረም ምክትል ዲኗ ሃሳብ አቀረበች:: ሊያደርጉት ከወሰኑ በኋላ መልሰው ተዉት:: እኔም ዩኒቨርስቲውን ልለቅ ካልኩ በኋላ መልሼ ተውኩት:: ከዚያ በኋላ ምርምሬ ላይ ብቻ አተኮርኩ:: ቀጥሎ የማውቀው ነገር ቢኖር ከሦስት ዓመታት በኋላ የቀድሞው አማካሪዬ መባረሩን፣ ለአንዳንድ ፕሮፌሰሮች ከባድ ማስጠንቀቂያ መሰጠቱን፣ በማኅበራዊ ሳይንስ ዘርፍ ልምድና ብዙ የምርምር ህትመቶች ያሉት ፕሮፌሰር መቀጠሩን እና አሜሪካውያን ያልሆኑ ተማሪዎችን ጉዳይ የሚያስተናግድ አዲስ ቢሮ መከፈቱን ነው:: በዚሁ ቢሮ አስተባባሪነት በተዘጋጀ ኮንፈረንስ የእኔ ወረቀት ከSchool of Education ተመርጦ እንዲቀርብ ተደረገ:: የጥናቱንም አቅጣጫ አንድ በአንድ እየተከታተሉ ስለነበረ እስኪያልቅ ድረስ ከእኔ ያላነሰ እነርሱም ጓጉተው የነበሩ ይመስላል:: ዲኑም በማናቸውም የጥናት ዘርፍ ከማናቸውም ሀገርና ብሔር የመጡ ተማሪዎችን ለማስተናገድ ኮሌጁ ዝግጁ መሆኑንና በኮሌጁ ያሉ ብዙዎቹ መምህራን ከmid-West ወጥተው የማያውቁ ዓለማቀፋዊ ልምድ የሌላቸው መሆናቸውን በመረዳት ከሁለቱም ወገን መግባባት እንዲኖር በመማጸን ንግግር አደረገ:: የዲኑና የምክትል ዲኗ እኔን የሚያዩበት አስተያየትም ልክ ኀዘን እንደሚደርስ ሰው ነበር:: በፈረንጅኛ "ይቅርታ" እያሉ እንደነበረ ስለገባኝ በነጭ የሰው ዘር ላይ ተስፋ ከመቍረጥ ለጥቂት ተረፍኩ::"ወገኖች" የምላቸው ኢትዮጵያውያን ወዳጆቼ ግን በነዚህ ዓመታት የነበርኩበትን ውጣ ውረድ እንደመልካም አጋጣሚ በመቍጠር በንግግርና በድርጊት ጉዳት ለመሰንዘር ያደርጉት የነበረው ጥረት እስካሁን ይቅርታ ለማድረግ እየታገልኩበት ያለ የማይረሳ አሳዛኝ የሕይወቴ ገጠመኝ ነው::

**ናይል:-** **የእረፍት ጊዜዎን በምን በምን ያሳልፋሉ? እንዴት?**

**ዶ/ር መስከረም:-** የእረፍት ጊዜዬን ብዙ ጊዜ መንፈሳዊ መጻሕፍትን በማንበብ አሳልፋለሁ::መንፈሳዊና ታሪካዊ መካናትን መጎብኘት ደስ ይለኛል:: ቤቴን ከጓዳ እስከ ሳሎን ግልብጥ አድርጎ ማጽዳትና ዕቃ ማጠብ በጣም ከሚያድሱኝ የእረፍት ጊዜ ማሳለፊያ መንገዶቼ መካከል አንዱ ነው - በተለይ ሙሉ ቀን ነጻ ሳገኝ:: በተጨማሪም የበለጠ ልረዳው የምፈልጋቸውን ርእሰ ጕዳዮችን የሚዳስሱ ፊልሞችን ፈልጌም ቢኾን ተከራይቼ በቍም-ነገር አያለሁ::

**ናይል:-** **በመጨረሻ ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ እድሉን እንስጥዎ?**

**ዶ/ር መስከረም:-** ኢትዮጵያውያን ቅን እንሁን፤ ቅንነትን እንጠብቅ እላለሁ:: ባህሪያችን እጅግ ተበላሽቷል:: መልሶ ሊያቃናን የሚፈልግ ኃይል ቢመጣ ሊሠራበት የሚችለው መነሻ እንኳ ስለሚያስፈልገው ጥቂት እንጥፍጣፊ ቅንነት ከውስጣችን እንዳይጠፋ አጥብቀን እንጠንቀቅ፤ ለሌላው በልባችን የምንመኘውንና በአፋችን የምንናገረውን እንወቅ እላለሁ::

**ናይል:-** **ዶ/ር መስከረም ስለነበረን ቆይታ በናይል ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ስም እናመሰግናለን!**

**ዶ/ር መስከረም:-** እድሉን ስለሰጣችሁኝ እኔም አመሰግናለሁ!

# Chinese Language Teaching Scheme

Dr. Wenxia Zhang
Confucius Classroom at BDU

The Chinese language teaching scheme was launched on March 24, 2014 by two Chinese instructors -- Mr. Haisheng Duan and a volunteer Mr. Changpan Shi. The first batch of learners was 25 teachers and 70 students who were grouped into three sections.

The program is the result of the cooperation agreement made between Bahir Dar University and Addis Ababa-based Confucius Institute of China. In light of this agreement, Confucius Institute Head quarter assigns Chinese instructors and volunteers according to the requirements of each teaching center.

Initially, the program was a Chinese language teaching point at BDU. With the support of the president of BDU, Dr. Baylie, the vice-president, Dr. Matebe, and with the great help of the program coordinator, Dr. Seyoum, the dean of the faculty of Humanities, and of course the support of each and every staff and student, now this program has been upgraded to Confucius Classroom in November 2015. The upgrading entitles us to applying for 1,000 copies of books donated by Confucius Institute Headquarters in Beijing, now we have finished the online application; the Headquarters are organizing our books and teaching materials. These books are expected to be shipped to Bahir Dar no later than the end of June.

On 22nd January, 2016 at the meeting of Dr. Matebe, Dr. Seyoum and Miss Shen, the director of Addis Ababa Confucius Institute, BDU leaders said that three classrooms will be granted for Chinese Language learning after the building located at Business and Economics campus is completed. Then a library room will be set up.

On 24th February, 2016 after lunchtime, Dr. Baylie, the president of BDU paid us a surprise visit, of course a pleasant and encouraging one. He talked about our future plan. He even drew the layout of the three classrooms. He enthusiastically asked us about our problems here at BDU and vowed to solve them. For example, when we informed him that we needed two tables to install the computers on, he immediately called the relevant department director so that the available computers were ready to put into use. He also made a proposal that a Chinese Food Culture Festival be held and he would link us to the hotel restaurant. Now the staff of Chinese Language Teaching Center (CTC) at BDU is making a detailed plan for the activity.

Now the Chinese Language and Culture Club is to be opened for all the staff and students. Many cultural and educational resources are stored in our electronic repositories. These materials are classified into photo gallery, Chinese music, Chinese movies, HSK, Chinese Learning downloaded and online sources and handicrafts. Each has many subdivisions, for example, the photo gallery includes pictures of scenic spots, Chinese cuisine, traditional Chinese apparel and characteristically Chinese architecture. Chinese music is sub-classified into popular songs, classic songs and folk songs, to list a few. Chinese movies contain Jackie Cheng and Jet Li and many other internationally well-known film stars. HSK is an internationally Chinese Language examination organized by the Chinese government. It grants students many priorities of applying for scholarship to go to China for MA and Ph. D. Also HSK provides the students with opportunities to take part in the Summer Camp, Winter Camp in Beijing every year.

The resource center has been designed to help students use the learning materials. It will also make maximum effort to accommodate and communicate with students so that their problems will be solved in time. To this end, teachers will always be available in the resource center for questions and extra help.

At the Club, the students will have good opportunities to learn how to make the Chinese Knot knitting, and learn to write Chinese calligraphy, and practice using chopsticks. In short, the Chinese Language and Culture Club located at Wisdom Tower situated on the 3rd floor (office number 304) is designed to be one where you can experience Chinese culture and learn Chinese well.



In light of these views, the staffs of the Chinese Language Teaching Center (CTC) of Confucius Classroom at BDU hold a strong belief that all the participants will benefit a lot from the training.



## CLT extends its Chinese language teaching program to HUAWEI at Bahir Dar

With the invitation of HUAWEI Mobile Company at Bahir Dar, we offer Chinese language education to the Ethiopian employees of this company since 20th, February. The class begins at 10:00 and ends at11:30 every Saturday morning. So far there are more than 15 locals who are taking the Chinese class three times. The Amhara Regional Executive Manager Mr. Li Pei said learning Chinese is good both for the local employees and for HUAWEI. It helps to build a better teamwork and to establish a more smooth communication. He hopes Chinese Language Teaching Center at Bahir Dar University can carry on the program.

# ህልም እልም

(ክፍል 2)

ቤተልሄም ሃይለማርያም
2ኛ አመት የኢኮኖሚክስ ተማሪ
www.facebook.com/betelhemhailemariam

“. . .ሄሎ” ከስልኩ ውስጥ ጎርናናው ድምፅ እያስተጋባ ነው፡፡ “አ. .አ. . .ቤት” ስልኩ ተቋረጠ፡፡ በህልም አለም ሲያሰቃያት የነበረው በውኗ የሚደገም መሰላት፡፡ እንደዛ ሲያቃጥላት የነበረው የገዛ ሰውነቷ የበረዶ ናዳ የወረደበት እስኪመስላት ብርድ ብርድ እያለ አንዘፈዘፋት፡፡ ከቅዝቃዜው የተነሳ እጅን እግሯ በድን የሆነ መሰላት፡፡ አያቷ “ሰው ሊሞት ሲል ይቀዘቅዛል” ያሏት ትዝ ብሏት የበለጠ ፈራች፡፡ ይህን ሁሉ በደል ተሸክማ እንዳትሞት ፈራች፡፡ ይህን ሁሉ ክፋት እንደተሸከመች እንዳትሞት ፈራች፡፡ እንኳን ፈጣሪ የምትቀበርበት አፈርም አላውቅሽም እንዳይላት ፈራች፡፡

“. . .አያትሽ” ነበር ያላት ደዋዩ፡፡ “አያቴ ምን? . . . ምናልባት ነገሩን ሁሉ ደርሶበት. . .” ለማሰብ ሞከረች “. . .ለፖሊስ ሊያሲዝዘኝ. . . በፍፁም በፍፁም አይደርስበትም፡፡ ቢደርስበትም አባባ እንደዚህ አይነት ውሳኔ አይወስንም፡፡”

አያቷን ታውቃቸዋለች የዋህነታቸው የምር ነው፡፡ አርቆ አሳቢነታቸውና ብልኸነታቸው ፈጣሪ ቅንነታቸውን አስቦ የሰጣቸው ፀጋ ነው የሚመስለው፡፡ ለሷ ግን እንቅፋት ናቸው፡፡ ሳያስቡት እጃቸው በገባ ሚስጢር ስትገነባው የኖረችውን ክብር በሰኣታት እድሜ ውስጥ ናደው፡፡ አዘነችባቸው፤ ጠላቻቸው፡፡ ከነሚስጥራቸው ልታስገድላቸው ወሰነች፡፡ ህይወት እንደዚህ ናት መልካምነት ሞትን የሚጋብዝባት መድረክ፡፡ “እና አባባ ሚስጥሩን ሁሉ እንደታቀፈ የዋህ ስጋው ከነፍሱ ተነጥላ ይሆን?” ግምቷ ራሷን አስደነገጣት፡፡ ያንን ሁሉ ከጥንስሱ እስከ ድፍድፉ ስታሴር ግን አልቀፈፋትም ነበር፡፡ “አባባን አስገድላ. . .” ሰቀጠጣት፡፡ ማማተብ ፈለገችና ፈጣሪ የማያውቃት ተኽኮለኛ መሆኗን ስታስታውስ ማማተቧ ጥቅም አልባ እንደሆነ ገብቷት ተወችው፡፡ ግድግዳውን ተደግፋ ቁልቁል ወደ መሬት ተንሸራተተችና ጉልበቷን አቅፋ ተቀመጠች፡፡ በእጇ ብዙ ሰው ደም ቢፈስም ጥፋጠኝነቷ ግን አልታይሽ አላት፡፡

ሁሉም ግን ወደ ዝና አደባባይ የሚያደርሳት መንገድ ላይ ጋሬጣ ሆነው የተገኙ ነበሩ፡፡ “የስኬትን ጉዞ ስትጀምር ጎዳናህን የሚያጠበውን፤ ሊቀድምህ የሚሞክረውን እንዲዘገይ ሳይሆን እንዲቀር አድርገው፡፡” የሚል መርህ አላት፡፡ መጡባት እንጂ አልሄደችባቸውም፡፡ “. . .እንዴ” አለች በድንጋጤ ተሳስሮ የነበረው ሰውነቷ ባንዳች ድንጋጤ እየተተረተረ፡፡ “ወይኔ ኤልሳ!” ተስፈንጥራ ተነስታ አስሩንም ጣቷን ፀጉሯ ውስጥ ከታ መፎከት ጀመረች፡፡ ቅዝቃዜዋ ወደ ግለት ተለወጠ፡፡ ተናደደች፡፡ “ወይኔ ልጅት አያደርገውማ፡፡ ግደይ ይህን አያደርገውማ፡፡” ራሷን የምታምነውን ያህል ግደይን ታምነዋለች፡፡ ሃይማኖተኛ ብጤ ስለሆነ ምናልባት ኩነኔ ፈርቶ ካልሆነ በቀር ለገንዘብ ብሎ አልያም እንደሷ ለዝና ብሎ እንደማይከዳት ታውቃለች፡፡ ግደይ ፊቱ ላይ ያለው ጠባሳ ጨካኝ አስመሰለው እንጂ ውስጡ ተቃራኒ ነው፡፡ የፈለገው ቢያዝንና ቢራራ ያንሁሉ ሚስጢር አጋርታው ወደኋላ እንደማይመለስ አሰበች፡፡ ግን ጠርጥራዋለች አያቷ እንደሚያሳዝኑት በተደጋጋሚ ነግሯታል፡፡ “ቢሆንስ. . . ኤልሳ አባቷን ግደልልኝ አለችኝ” ብሎ ሊነግራቸው፡፡ ለነገሩ ቢነግራቸውም አያቷ “ልጅ ስለሆነች ነው እንጂ ለክፋት ብላ አይደለም” እንደሚሉ ታውቃለች፡፡ ልጅ ስለሆንሽ ነው እያሉ ነው እዚህ ሁሉ በቀል ውስጥ የከተቷት፡፡

ስልኩን አፍጥጣ ተመለከተችው፡፡ በድጋሚ እንዲህ የምተለምነው ይመስል እስሩ ሄዳ ተንበርክካ መጠበቅ

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

# የግጥም ጥግ

## የግሉኮስ... ጠብታ

በችግር ተጠብሳ... ችጋር አጠውልጓት
የጦርነት አረር... ውስጧን እየፈጃት
ገመምተኛ ሆና ስትጠናወስ
ስታጣጥር ሲያይዋት ተይዛ በነፍስ
ላይገላት ጨርሶ... ወይም ላያድናት
ምርቅና መረቅ ነው የሚዘረጉላት፡፡
ጠብ... ጠብ... እያለ የሚወርድ በጅስሟ
የአውሮፖ እርዳታ ነው የሆናት ለስሟ
አፍሪካ... ታማሚ
አፍሪካ ... ታካሚ
አፍሪካ ...አትድን አፍሪካ አትፈወስ
ከጠብታ በቀር የለ ሞልቶ ሚፈስ
ለአፍሪካ መርገም ነው የአውሮፖ ግሉኮስ፡፡

## የሀገር አራሙቻ

ከ2፡30 እስከ 6፡00 ሰዓት

ባለ ጉዳይ፡- ጤና ይስጥልኝ እመቤቴ፣
ጉዳይ ኖሮኝ ነበር ቢሮሽ መገኘቴ፣
ገብቼ ላናግር; ክቡር አላፊውን፣
አልቆይም አንድ አፍታ እወጣለሁ አሁን፡፡

ፀሐፊዋ፡- ይቅርታ ባለ ጉዳይ... ሀላፊው አልገቡም፣
የግል ጉዳይ ኖሯቸው ለጊዜው አልመጡም፣
የግድ ከሆነ እርሳቸውን ማግኘት፣
ይገቡ ይሆናል ምን አልባት ከሰዓት፣
ያን ጊዜ ተመለስ ታገኛቸዋለህ፣
እነግርልሃለሁ መጥተህ እንደሄድህ
7፡30 እስከ 11፡00 ሰዓት.....፡፡

ባለ ጉዳይ፡- አስታውሰሽ እመቴ ጠዋት መጥቼ ነበር፣
ከሰዓት ብለሽኝ መጥቻለሁ ሳልቀር፣
የያዝኩት ጉዳይ የኔ ብቻ አይደለም፣
ብዙዎች ወክለውኝ ተሰምቶኛል ሸክም፣
ልግባ; ሀላፊው ዘንድ አንዴ ላናግራቸው፣
መፍትሄ እንዲሰጡኝ ሁሉን ላስረዳቸው፣

ፀሐፊዋ፡- ው...ው..ይ ምን አባቴ ላርግህ፣
ምናለ ቀደም ብትል ለትንሽ ዘገየህ፣
ክቡር ሃላፊያችን ስበሰባ ይዘዋል፣
ለዛሬ አልተቻለም ምን አልባት....
ነገ ከነገ ወዲያ ብትመጣ ይሻላል፡፡

ታዛቢው፡- በአንዳንድ መስሪያ ቤት ያለው ውጣ ውረድ፣
ሀገር አሳሪ ነው በድህነት ገመድ፣
ሳይሰሩ ግምገማ.... ሳይኖሩ ስብሰባ፣
ባለ ጉዳዩ በጐን... እሮሮና እንባ፣
መንግስት በሚዲያ #መልካም አስተዳደር»፣
እመጣለሁ ብሎ ጠዋት ማታ መዘመር፣
እስከ መቼ ድረስ በዚህ ይዘለቃል፣
በየቢሮው ያለውን ክፉ አራሙቻ፣
ነቅሎ መጣል ያሻል፡፡

በደስታ ተከስተ (ባሕር ዳር ዩኒቨርስቲ ፀጥታ አገልግሎት)

## ስማኝ ሰማይ

በል ስማኝ ሰማይ
ሁሉን እምታይ
ምድር ከጫካ ተሻርካ
ብትደብቅ የኔን ሲሳይ
ጨረቃ ብትሽኮረመም
ብትሸሽግ በፅልመት ላታሳይ
ፀሐይም ብትኮራ
ካደረችበት ባትመለስ ባትታይ
ግድ የለም!
በል ስማኝ ሰማይ
ቁልቁል ተመልከት አፋልገኝ
ከተነጠፍከበት ሆነህ ከላይ
ከ'ቅፌ ከወጣች ሰዓታት አለፉ
ከዓይኖቼ ከራቀች ሴኮንዶች ጎረፉ
ናፍቆኛል አንገቷ ክንዴ ያረፈበት
ናፍቆኛል ከንፈሯ ነፍሴ የጋለበት
በል ስማኝ ሰማይ
ሁሉን እምታይ
ሹክሹክታዋ ይሰማኛል
ማየቱን ግን ተስኖኛል
በል ስማኝ ሰማይ ወዳጄ
ሽቅብ የማይህ አንጋጥጬ
የምማፀንህ አጎብድጄ
ግለጥልኝ 'ባክህ ካለችበት ፈልግና
አልያም እንዳልቀር ሆኜ መና
በል ስማኝ ሰማይ
ሁሉን እምታይ፡፡

አረጋዊ ሰሎሞን (AS)
2008 ዓ.ም አ.አ

## Photo Gallery



BDU signing Memorandum of Understaning (MoU) with Gambela University



BDU's top management and intellectuals talk about BDU-VLIR-VOS-IUC program

To follow the latest news about BDU, check out our website:-
**http://www.bdu.edu.et**
facebook page:-
**www.facebook.com/bduethiopia**